# ግንቦት ሰባትን ደግፌ 8 ዓመት ተጓዝኩ - ከፃፍኩት የቀጠለ

መስከረም 21ቀን 2017ዓም

ውድ አንባቢያን! ቀደም ሲል ግንቦት ሰባትን ደግፌ 8 ዓመት ተጓዝኩ በሚል አርዕስት ከፃፍኩት የቀጠለ ፅሁፌ ይኸውና ተከታተሉት፣

ምንም እንኳን ሥለ ብርሀኑ ነጋ(ዶክተር) ገና ከኢሕአፓ ሾፌርነቱ ፣እሥከአሜሪካ ቆይታው እንዲሁም ወያኔ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ደግሞ ከአሜሪካ ወደኢትዮጵያ ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ የማውቃቸው ነገሮች ቢኖሩም፣አንዳንድ መረጃዎችን እሥካሟላ ድረስ፣ለተወሰኑ ወራት ከድርጅቱ ጋር እንደምቆይ መፃፌ ይታወሳል።ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰኑት ወራት ብዘገይም፣ይኸውና ተመልሼ መጥቻለሁ።

ብርሀኑና መሰሎቹ የሚሠሯቸው ወንጀሎች ብዙዎቹ ግልፅና በየሜዲያው ሥለሚታወቁ ወደዚያ አልገባም።ነገር ግን አንዳርጋቸውን አሥመልክቶ ምን ያህል ሕዝቡ እንደሚያውቀው ባላውቅም ጠቅሸው አልፋለሁ። አንዳርጋቸው በወያኔ ከመጠለፉ ከተወሰኑ ወራት በፊት ከሻዕቢያዎች ከእነኮሎኔል ፍፁም ጋር በአሠራር ሥለተጋጨ፣ሎንዶን ሄዶ ይቀመጣል። ይህ በዚህ እንዳለ ሻዕቢያዎችም ከብርሀኑ ጋር በተደጋጋሚ ይነጋገራሉ።ብርሀኑም አንዳርጋቸውን ለማግባባት ቢሞክርም አልተሳካም።ከዚህ በኋላ ሻዕቢያና ብርሀኑ በጋራ አቀነባብረው፣ሻዕቢያ ራሱ ለአንዳርጋቸው ደውሎ ይቅርታ ጠይቆ፣አንዳርጋቸው ወደኤርትራ እንዲመለስና ሥራውን እንዲሠራ ያግባባውና ይሥማማል።አንዳርጋቸው የአይሮፕላን ቲኬት የቆረጠበት አይሮፕላን እንዲያመልጠው ተደርጎ፣ሌላ አይሮፕላን ይዞ ወደየመን እንዲሄድ ተደረገ።በዚህ ጊዜ የየመን ድህንነቶችና የወያኔ ሠዎች የመን ጠብቀው አንዳርጋቸውን ሊወስዱት ችለዋል።ይህ እንደሚሆን ብርሀኑና ሻዕቢያ በሥምምነት የሠሩትና የሚያውቁት ነው በሚል የተወሰነው የግንቦት ሰባት ደጋፊ ይጋራዋል።ይህ በዚህ ተቋጨ።

ብርሀኑ(ዶክተር) ከኢሕአፓ ሾፌርነት ጀምሮ በጀብሃ፣ በአሜሪካና በኢትዮጵያ ቆይታው

እሥከዛሬ በግልፅ የማይታወቁ፣ከቅንጅት በፊትም ሆነ በቅንጅት ወቅት የዛሬው የግንቦት ሰባት መሪና መሰሎቹ ያደረጓቸውን ደባዎች፣ ባለማወቅና ባለመረዳት በቅንጅት ወቅት የተከተለውም ሆነ በግንቦት ሰባት የሚከተለውና የተዘናጋው ሕዝብ እንዲያውቀው ማድረግ ተገቢ ነው ብዬ ሥለማምን ይኸውና በጥሞና ትከታተሉት ዘንድ እጋብዛለሁ ።

ማሳሰቢያ! (1ኛ)ይህንን ፅሁፍ የምታነቡ ወገኖች በቅድሚያ እንድታውቁት የምፈልገው አሁን ብርሀኑ በግንቦት ሰባት ሥም የሚሠራውን አጥፊ ተግባር፣ በቅንጅትም ጊዜ የሰራውና ቅንጅትን መቀመቅ የከተተበት ሥለሆነ፣በፅሁፉ ውስጥ ብዙ ዕውነታዎችን ለመግለፅ ሲባል፣ፅሁፉ ሊረዝም በቅቷል። በየቀኑ እየከፋፍላችሁ እሥከመጨረሻው ካነበባችሁት ብቻ ነው፣ የብርሀኑንና የመሰሎቹን ምንነት በተመለከተ ሙሉ ግንዛቤ ልታገኙ የምትችሉት።

(2ኛ)ከሰዎች ሥሞች ጋር በመደጋገም የሚጠቀሱትን አቶ፣ወይዘሮ፣ወይዘሪት፣ኮሎኔል፣ዶክተር፣ኢንጂነዬር፣ፕሮፌሰር ወዘተ የመሳሰሉትን አንድጊዜ በቅንፍ ውሥጥ ካሥቀመጥኩ በኋላ፣በሥማቸው ብቻ እንደምጠቅሳቸው አንባቢ በቅድሚያ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ።

(3ኛ) በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ሥማቸው የሚጠቀሱ ሰዎች የሠሯቸውና ያደረጓቸው ነገሮች፣በተለያዩ አጋጣሚዎች የተገኙ፣ከራሳቸውም ፅሁፍ፣ንግግር፣እና ቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም ከነበሩባቸውና ካሉባቸው ድርጅቶች ጋር በተያያዘ የተገኙ ጭምር ናቸው።

(4ኛ)በመጀመሪያ ቅንጅት ከመፈጠሩ በፊት ብርሀኑ "እንዲህ ነበርኩና አደረግሁ" የሚላቸውን ከትችት ጋር በማያያዝ በአጭሩ ጠቃቅሼ፣በመቀጠልም በቅንጅት ወቅት የነበረውንና ያደረገውን ለብዙዎቻችን ያልተገለፀውን ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

ክፍል1

ብርሀኑ የ1966ቱን አብዮት በተገናኘ በ18ዓመቱ ኢሕአፓን እንደተቀላቀለ እና በ1969ዓም ወደበርሃ እንደገባ፣የድርጅቱ ሾፌር ሆኖ ፣ወሬ በማዛመትና በሠላይነት ሥለተጠረጠረ፣ ኢሕአፓ "አንጃዎች" ናቸው ያላቸውን አጋልጦ ለማሰር፣አንዳንድ የማውጣጣት መንገዶችን ድርጅቱ ሲጠቃቅስ፣ከሾፌርነት ባለፈ ጠበንጃ ጨብጦ የማያውቀው ብርሀኑ ተደናግጦ"ሳይጠሩት አቤት" በማለቱ "ኃጢያቱ በአደባባይ ተገለፀ" በሚል በድርጅቱ "ለአጭር ጊዜ ሸብ" ተደርጎ ተባሯል። ከተባረረም በኋላ በእግር አውጭኝ፣ያገኘውን መንገድ ይዞ የዕውር የድንብሩን ሲሄድ ፆረና ደረሰ።እዚያም እንደደረሰ

የጀብሃ አካባቢ በመሆኑ ለጀብሀ(ለኤርትራው የአስማን ሳላህ ሳቤ እሥላማዊ ድርጅት) እጁን ሠጥቶ፣ለሰባት(7)ወር ተኩል ጀብሃ አረም ሲያሳርመው፣ውሀ ሲያስቀዳው፣እንጨት ሲያስለቅመው፣ግንድ ሲያስፈልጠው፣የእህል ጆንያ ሲያሸከመውና ሲገለገልበት ይቆያል።

አንድ ቀን የጀብሃ ደህንነት ኃላፊዎች ግምገማ ሲያካሂዱ "ብሶት" መኖሩንና አለመኖሩን ለማወቅ "በሚል እየዞሩ ሲያናግሩ ብርሀኑ ጋ ይደርሳሉ።

ብርሀኑም "ምግብ ያንሰኛል፣ይርበኛል "፣ካለ በኋላ ቀጠል አድርጎ " የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የእናንተን ትግል ደግፈው በኃይለስላሴ ላይ ሲያምፁ፣የዕድሜ ጎልማሳነት ሳይገድበኝ አቋሜ ከተማሪዎቹ ጋር ነበር። ዛሬም እንደምታዩኝ የደርግን መንግሥት ተቃውሜ፣ የእናንተን ትግል ደግፌያለሁ" ይላል።

መቼም ወሬና የወሬ ጉቦ የሚወድ ሠው በየሄደበት እንደቀላዋጭ ውሻ እንደተካለበ ነው።ግምገማውን የሚያካሂደው ሰውዬ ግምገማውን ካጠናቀቀ በኋላ ምንም ሳይለው ትቶት በሄደ በሳምንቱ ምን እንዳገኘበት አይታወቅም ከማሰር ማባረርን መርጦ ያባረዋል።ከዚያ ወደ ሱዳን፣ከሱዳን ወደ ወደአሜሪካ ይጓዛል።

በአሜሪካ ቆይታውስ ምን አደረገ?

ኃያላን ነጮች ምሥራቅ አፍሪካን ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ኤርትራ ከመገንጠሏ ቀደም ብሎ "የአፍሪካ ቀንድ" የሚል ሥም በመስጠት ሶማሌን፣ኢትዮጵያን ፣ሱዳንን፣ኬንያን፣ወዘተ በአንድ በጋራ ሥም ለመጠቅለል ያዝ ለቀቅ እያደረጉ መሠሪ ሥራ ሲሰሩ እንደኖሩ የአደባባይ ምሥጢር ነው።ወደፊትም ደካማ ሆነን ከተገኘን እንደማይቀርልን አልጠራጠርም።

ታዲያ ብርሀኑ ነጋ ከነጮቹ ጋር ያለው ግንኙነት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በእጅጉ እንደጎዳው ባልጠራጠርም፣አሜሪካ ኒዮርክ በነበረበት ጊዜ፣ዛሬ በአንድነት ሥም እንደሚመፃደቀው ሳይሆን፣

የኢትዮጵያን ጠላቶች የሶማሌን፣የሱዳንንና የኤርትራን ተገንጣይ ምሁራን ተብዬዎች ሰብስቦ "የአፍሪካ ቀንድን" አቁቁሞ ለአምሥት (5)ዓመት ኮንፈረንስ በማካሄድ የኢትዮጵያን አንድነት በእጅጉ ሲሸረሽር ኑሯል። ከኢትዮጵያ ጠላቶች ከእነሻዕቢያ፣ወያኔና ኦነግ ተገንጣዮችም ጋር የሚተዋወቀው በዚህ ወቅት እንደነበር ግልፅ ነው።ዛሬ ከወያኔ እንደራቀ ቢናገርም፣ ከሻዕቢያና ከኦነግ ጋር ግን እንደተጋባ መቀጠሉን ዓለም ያውቀዋል።

ብርሀኑ ከኒዮርክ ወደፊላደልፊያ ሲሄድና የተገንጣዮቹም ተልዕኮ ሲፈፀም "የአፍሪካ ቀንድም" አንቀሳቃሽ አጣ። ፊላደፊያም ሄዶ ከአገር አፍራሾች ጋር "እምቢልታ" የሚል መፅሔት ለጥቂት አመታት ቢሞክርም በአጭሩ ተቀጭቷል።

ይህ በዚህ እንዳለ የትግሬ ወራሪ ቡድን አዲስ አበባ ከገባና ኢትዮጵያን ገነጣጥሎ፣በ9(ዘ)ባንዲራና በዘር ካዋቀረ በኋላ፣ወራሪው ትግሬ ከኦነግና ከሻዕቢያም ጋር ትብብሩን ቀጥሎ ቀደም ሲል የጀመረውን አጠናክሮ የአማራን ዘር በወልቃይት፣በራያ፣በሐረር፣በአሩሲ ወዘተ እያደነ፣በወንጀል ላይ ወንጀል እየሰራ እንደሆነ ጎልቶ በወጣበት፣ሕዝብም በገፍ ወደውጭ በሚሠደድበት ወቅት፣ አልፎ ተርፎም "የትምክህተኞችን ጎራ ማፈራረስ አለብኝ" በማለት የዩኒቨርሲቲን 42 መምህራንን( 41 አማራዎች እና አንድ ቅይጥ) ከሥራ ባፈናቀለበት ወቅት "ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች"እንዲሉ፣ብርሀኑ ከአሜሪካ ገሥግሶ ወደወያኔ ተጓዘ።

ብርሀኑ ወደወያኔ መሄዱንም አሥመልክቶ እንዲህ ሲል ይነግረናል፣

(1ኛ)" ከ15ዓመት የአሜሪካ ቆይታዬ በኋላ ጓዜን ጠቅልዬ ኢትዮጵያ ገባሁ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደማስተምር አውቄ ለማስተማር የሚሆኑኝን መፃሕፍትና ቁሳቁስ በብዛት ተሸክሜ ነበር የተመለስኩት።ከተማርኩት ትምህርት አንፃር በኢኮኖሚው መስክ በመሳተፍ የተሻለ አሥተዋፅዖ ይኖረኛል የሚል ፅኑ ዕምነት ሥለነበረኝ" ይላል።

-ሌላው ቢቀር ብርሀኑ በመምህርነቱ በወያኔ ከሥራ ከተፈናቀሉት 42ቱ (ፕሮፌሰር አሥራትን ጨምሮ) መምህራን ጎን በመቆም ልባዊ ትብብሩን(ሶሊዳሪቲ) ከማሳዬት ይልቅ አሜሪካንን ጥሎ ወደኢትዮጵያ ተንደርድሮ ሄዶ የመምህራኑን አንድ ቦታ መውሰድና ለወያኔ ተባባሪነቱን(ሶሊዳሪቲ) ማሳየቱና አብሮ መቆሙ የቅርብ ጊዜ ሆድ የሚያደማ ትዝታ ነው። እንዲህ ዓይነት አረመኔነትና ራስ ወዳድነት የተሸከመ ሰው ዛሬ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ዕውነተኛ ገፅታውን በአፈ ጮሌነት ደብቆ በመቧረቅ ሠዎችን ሲያሳስት ማዬት ያቆስላል። ለነገሩ እኔንም አሳስቶኝ ነበር።

ብርሃኑ ቀጠል አድርጎ እንዲህ ሲል ያሥነብበናል፣

(2ኛ) "አብዛኛው ሕዝብ ተቃዋሚዎቹ (እነወያኔ ኦነግ ወዘተ ማለቱ ነው) ያነገቡትን የተሳሳተ ዘውጌያዊ አመለካከታቸውን ሥልጣን ከያዙና ከተደላደሉ በኋላ ይተውታል በሚል ዕምነት እንደደገፋቸው፣ በተቃራኒው ግን በከረረ ሁኔታ የሚቃወሙ በቁጥርም ሆነ በአመለካከት አናሳዎች እንደነበሩ" ይነግረናል።

-እነኚህን ከዕውነት የተጣሉ አነጋገሮች አንድ በአንድ እንዳሥሳቸው።

(ሀ) ” ሥልጣን ከያዙና ከተደላደሉ በኋላ ይተውታል በሚል ዕምነት አብዛኛው ሕዝብ ደገፉቸው” የሚለውን አነጋገር በተመለከተ “ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል” ከመሆን አያልፍም።ሥልጣን ሥለያዘ ዓላማውን የሚለውጥ ቡድን የትም ዓለም ታይቶና ተሰምቶም አያውቅም።ብርሀኑ የኖረበትን ትልቅ የዲሞክራሲ አገር የሚባልለትን አሜሪካንን እንኳን እንደአንድ ምሳሌ ብንወስድና ከቅርቡ “የዴሞክራት ፓርቲ” ሰው ከሆነው ከክሊንተን ብንነሳ፣ የአሜሪካ ሕዝብ መርጦት “ሥልጣን ይዞ ከተደላደለ በኋላ ቀደም ሲል ይዞት የመጣውን የዴሞክራት አቋም አልተወውም”፣ያንኑ ነው ለማሥፈፀም የጣረው።አባማንም ሆነ የዛሬውን ትራምፕን ብናይ ይዘው የተነሱትን ለማሥፈፀም ነው ደፋ ቀና ሲሉ የተስተዋሉትና የሚሥተዋሉት።ታዲያ ብርሀኑ ወያኔም ይዞት የመጣውን እንደሚያሥፈፅም ሃቁን አጥቶት ሳይሆን በማምታታት ጥቅሙን ለማስጠበቅ ያደረገው ግርግር ነው ብንል ይቀላል።እኛ ለብርሀኑ ያለን ብቸኛ መልስ “አውቀንብሀል፣ነቅተንብሃል” ነው።

(ለ) ብርሀኑ ተቃዋሚዎች የሚላቸውን ወያኔን፣ኦነግንና መሰሎቻቸውን “አብዛኛው ሕዝብ” ደግፏቸው አያውቅም። በመሳሪያ ሥለመጡበት የተሻለ ወይም የባሰ አገዛዝ ይሁን አይሁን የሚያውቀው ነገር ሥለሌለ ፈጣሪን እየተማፀነና የተሻለ ያምጣልን በማለት ቆሞ ተመልካች ነበር የሆነው።ሃቁ ይህ ነው።

(ሐ )በከረረ ሁኔታ የሚቃወሙ ብርሀኑ እንደሚለው አናሳዎች ሳይሆኑ በቁጥርም ሆነ በአመለካከት ብዙዎች ነበሩ፣ግን መሳሪያ ባለመታጠቃቸው፣ለብርሀኑ የብዙ ጥቂት መስለው ሊታዩት ችለዋል።

-ብርሀኑ እርሱ እራሱ በክፉም በደጉም የሚያውቀው ቅንጅት ምርጫውን ያሸነፈው አናሳ ተቃዋሚ ሆኖ ነው እንዴ?

ወይስ እንደብርሀኑ አባባል “የወያኔ ደጋፊ የተባለው አብዛኛው ሕዝብ” ብርሀኑ ከወያኔ ጋር በሥራበት ወቅት፣ “የወያኔ ደጋፊ የነበረ።ብርሀኑን ወያኔ ፊት በነሳው ጊዜ ብርሀኑን ተከትሎና ደግፎ በመነሳት የተቃወመ ነው።” ሊለን ይሆን?

ዕውነታው ግን አንድ ብቻ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኋላም ቅንጅትን የደገፈውም ጭምር፣ ከሥር ከመሠረቱ የወያኔን የዘር ፖለቲካ ተቃዋሚና የኢትዮጵያ አንድነትን ደጋፊ ነበር ።ሀቁ ይህ ነው።

(3ኛ)ብርሀኑ በመቀጠል እንዲህ ይለናል “በጊዜው በኤርትራ መገንጠል የተበሳጩ ብዙ አገር ወዳድ ኃይሎች ቢኖሩም ተገዳላዮቹ(ወያኔዎች) በነበራቸው ጨዋነትና ሰው አክባሪነት ህብረተሰቡን ከወንጀል ለመከላከል የወሰዱት እርምጃ ድጋፍ አሥገኝቶላቸዋል”ሲል ካተተ በኋላ “ይህን ሁሉ አዎንታዊ ገፅታቸውን በማዬት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት “ቅኖች ናቸውና ባለማወቅ እንዳይሳሳቱ እንርዳቸው” በሚል ብዙ የፖለቲካ ሰዎች እንደተቀላቀሏቸው ይነግረናል።ቀጠል አድርጎ ደግሞ ”ኢሕአዴግ ከመሠረቱ በአመለካከትም ሆነ በተግባር በትግል ላይ እያለም፣ዲሞክራሲን በሚመለከት፣በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የብሔር ብሔረ ሰብ ጥያቄና አፈታቱን በሚመለከት፣በኤርትራ ጉዳይ ወዘተ መሠረታዊ ችግሮች ያሉበት ድርጅት መሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ”” ይለናል።

ክፍል2

-ይህ ሠው “አልሸሹም ዘወር አሉ” ካልሆነ በስተቀር “ቅኖች” ለሚላቸው አገርና ሕዝብ አጥፊዎች ሙሉ ድጋፉን ሠጥቷቸው ኑሯል።

(4ኛ)“ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዝ የወሰዳቸው አንዳንድ እርምጃዎች(ለምሳሌ ለዲሞክራሲ ያሳይ የነበረውን ወገንተኝነት ማለትም መጀመሪያ የወጣው የፕሬስ ሕግ፣በነፃ ጋዜጦች ይወጡ የነበሩ መንግሥትን ክፉኛ የሚኮንኑ ፅሑፎች፣ዓለም አቀፍ ሕግጋትን በሕገ መንግሥቱ ውሥጥ ያካተተ ሕገ መንግሥት መውጣቱን የገባያ ኤኮኖሚን፣ነፃ ፕሬስ መፍቀድ ወዘተ)ድርጅቱ ሁኔታዎችን አይቶ ሊቀየር ይችላል” ብሎን አረፈው።

-ይህንን ፅሁፍ በደንብ ከተከታተልነው ቀደም ሲል እንዳልኩት ”ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት”ይሏታል ነው።

- በተራ ቁጥር3 መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ የተናገረው እርስ በእርሱ መቃረኑ ሲደንቀን፣ በተራ ቁጥር 3 መጨረሻ የተናገረውን እንደገና በተራ ቁጥር 4 ላይ በመቀልበስ እርስ በእርሱ የሚላተምና የሚጋጭ አድርጎታል።

-ልብ ያለን ልብ እንበል! ወያኔ ከመጀመሪያ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ሳይሆን የትግሬ ነፃ አውጭ ብሎ እንደታገለና ሥልጣንም እንደያዘና እንደቀጠለበት አሳይቷል።ይህንን አገርና ሕዝብ አጥፊ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ አሠራሮችን፣ታክቲኮችን፣ማዘናጊያዎችን፣ማታለያዎችን መጠቀም ነበረበት፣በመሆኑም ለአመነበት አገዛዝ እንዲያመቸው፣

(ሀ)በተለያዩት ነገዶችና ጎሳዎች ሥም ድርጅቶች አቋቋመ፣ (ለ)ዓለምንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል ተግባር ላይ የማይውል በወረቀት ላይ የሚውል ዓለም አቀፍ ሕግጋትን ያካተተ ሕገ መንግሥት አወጣ፣ (ሐ)የፕሬስ ሕግ አወጣ፣ነፃ ፕሬስ እንደፈቀደ አሥመሰለ፣የነፃ ጋዜጦች ፅሑፎች ወያኔን እንዲኮንኑ መንገድ የከፈተ አሥመሰለ፣ የገባያ ኤኮኖሚንም

በተመለከተ እንዲሁ አደረገ። በእነኚህና በሌሎችም መሠሪ አካሄዶች ተጠቅሞ ዕድሜውን ባራዘመ ቁጥር የሚፈልጋቸውን ተግባሮች ከፍፃሜ ለማድረስ ይጠቅመዋል።ይህ ለማንኛችንም በተለይ ተምረናል ለምንለው ወገኖች ትናንትም፣ዛሬም ግልፅ ነው።

ብርሀኑም እንደወያኔ በዘር የሚያምን ካልሆነ በስተቀር "የትግሬ ነፃ አውጭ" በሚል ለአንድ ለትግሬ ብቻ የቆመ ቡድን ሥለዴሞክራሲ፣ ሥለዓለም አቀፍ ሕግ የደነገገውን፣ለማዘናጊያና ለማስመሰል የተጠቀመባቸውን አካሄዶች ጥሩ እንደነበሩ ባላሥተጋባ ነበር።ገና ከጅምሩ የትግሬ ነፃ አውጭነትን ሥም የያዘው ወያኔ ዓለም አቀፍ ሕግጋት ብሎ ሲነሳ፣ ብርሀኑም እንደሌሎቻችን ወያኔን "የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ" ብሎ በቆራጥነት መታገል ነበረበት እንጅ ለወያኔ ሕገ መንግሥት ዕውቅና በመሥጠት ተገዥ ሆኖ መቆዬት አልነበረበትም።

ታዲያ የትግሬው ዘረኛ ቡድን ኢትዮጵያን በዘር ከፋፍሎ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ምልክት የሆነውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሠንደቅ ዓላማችንን አጥፍቶ፣ በ9(11) የመንደር ባንዲራዎች የተካ፣ዕውነተኛ ገፅታው የዘር እንጅ የአንድነት ያልሆነ ቡድን መሆኑ እየታወቀ ፣ብርሀኑ! ከአሜሪካ ገስግሶ ሄዶ ወያኔዎችን ዴሞክራቶች እንደሆኑ በመሳልና

በማጀብ፣የወያኔን በማር የተጠቀለለ መርዝ እየረጨ ሲያጠናክርና ሲያስገድለን መኖሩን እንደትክክለኛ ተግባር እንደማንቀበለው መረዳት እንዴት ተሳነው?

"በ1966ዎቹ ከመካፈልም በላይ በኢሕአፓ ውስጥ አልፌአለሁ፣ንቃቱ አለኝ" የሚለን ብርሀኑ፣እንዴት በዘር ተደራጅቶ የመጣን ቡድን ዲሞክራት ነው ብሎ ሊነግረን ደፈረ? እንኳን በፖለቲካው ዓለም ያለፈ ይቅርና ማንም ፖለቲካ ሲያልፍ ያልነካው ወገን፣ወያኔ የትግሬ ነፃ አውጭ ድርጅት እንጅ የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ድርጅት አለመሆኑንና ለኢትዮጵያ እንዳልቆመ አያጣውም።ከዕውነት በተቃራኒው የቆመን አካሄድ ዕውነትነት እንዳለው አድርጎ ማቅረብ ሕዝብን ግራ በማጋባት፣ወያኔን ለማጠናከር ካልሆነ በስተቀር ለሕዝብ የሚያመጣው ጥቅም አይኖርም።

ወያኔ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በመሳል የወያኔን ሥህተት ለመቅረፍና ለመደበቅ ዙሪያ ጥምጥም ከመሄድ ይልቅ "የወያኔን የዘር አካሄድ እኔ ብርሃኑ ሥላመንኩበት ብሎም ሥለምደግፈው በዚያው ወያኔ በመጣበት የዘር መንገድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሊያጎለብት ይችላል " ቢል ይቀላል። ከወያኔ ሠዎችም ጋር እጅና ጓንት በመሆን የመቆዬቱም ምክንያት ይኸው ነው ።

ወያኔ! ብአዴን የአማራ፣ ኦህዴድ የኦሮሞ፣ የእነካሱ ኢላላን ድርጅት የደቡብ፣ ወዘተ.. እያለ ጎሳዎችን የተለያዬ ባንዲራ አሸክሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዴሞክራቲክ ግንባር (ኢሕአዴግ) የሚል የኢትዮጵያን አንድነት እንደሚወክል አሥመስሎ በማቅረብ 26ዓመት እንዳዘናጋን፣የተለያዩትን ጎሳዎች በረቀቀ መንገድ በመቅረብ በአማራው ላይ አዝምቶ እንዳስጨረሰ፣እርስ በእርስም እንዳባላንና አገሩንም እንዳፈራረሰ የምናውቀው ሀቅ ነው።

"ህብረተሰቡን ከወንጀል የሚከላከሉ ቅኖች፣ጨዋዎችና ሠው አክባሪዎች ሥለሆኑ እንርዳቸው" ካለ በኋላ ወረድ ብሎ ደግሞ "መሠረታዊ ችግሮች አሉባቸው" ይለናል።እንደሚታወቀው ብዙ የሚያወሩ ሠዎች፣ከንግግራቸው ብዛት ሥህተቶችም በዚያው ልክ ከአፍ ይሾልካሉ። ብርሃኑም ብዙ ሥለሚያወራ፣አንዳንድ ጊዜ ወያኔዎች ወደማይፈልጉት እላፊ ውስጥ ሲገባ ግሣፄ ቢደርስበትም፣አምርረውበት ግን አያውቁም ነበር።ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1993ዓም ከሌላው ፀረ-አማራ ከመሥፍን ወልደማርያም(ፕሮፌሰር) ጋር ለ29ቀናት እሥር ቤት የቆዩት (በኋላ ላይ ቅንጅት ውስጥ የተካተተው "ኢዴሊ" የተባለው የእነኢዮኤል ድርጅት ወረቀት ከመስፍንና ከብርሀኑ ቤት በመገኘቱ ነበር) "በህቡዕ ድርጅት ፈጥራችኋል" በሚል ወያኔ ከቁጥጥሩ እንዳይወጡበት ያደረገው ትንሽ ቅጣት ነበር።

እሥር ቤት እንደገቡም በመጀመሪያው ሳምንት የአንድ የ80ዓመት ሽማግሌ ኦሮሞ የብርሀኑን ቀልብ ሥለሳቡት ቀርቦ በምን ምክንያት እንደታሰሩ እንደጠየቃቸው።እሳቸውም "ኦነግ ናችሁ እየተባሉ ያላንዳች ማስረጃ እንደሚታሰሩና እንደሚገረፉ፣የኦሮሞ ሕዝብ በፍፁም እየተማረረ እንደሆነ፣ራሳችንን እንደኢትዮጵያዊ ዜጋ ማዬት የማንችልበት ደረጃ ድረስ እየተገፋን ነው ።ጥላቻም እያደገ እንዳለና በዚህ ከቀጠለ ሕዝቡ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ስሜቱ ራሱ ጭራሽ እየተሸረሸረ በቅኝ ግዛት ሥር የሚኖር ያህል እየተሰማው እንደሚሄድ" በዝርዝር እንዳጫወቱት ብርሀኑ ያትትና ቀጠል አድርጎ ደግሞ በዚሁ እሥር ቤት እነ እሡዬ አብርሀ መጥተው እንደተቀላቀሏቸው፣ከብርሀኑም ጋር በኦነግ ሥም ሥለታሰሩትና አገሪቱ ወዴት እየሄደች 7

እንደሆነና “ይህ ችግር በቶሎ ሠላማዊ መፍትሄ ካላገኘ በኋላ ልንወጣው የማንችለው አዘቅት ውስጥ እንወድቃለን ብለን ተማመን” ብሎ ብርሀኑ ያትታል። ብርሀኑ ቀጠል አድርጎ ደግሞ አንድ ገጠመኝ ልናገር ይላል።ይኸውም “እሥር ቤት እንደገባን ሌሊት ላይ የተደበደበ ሠው ጩኸት እንሰማ ነበር።በመጀመሪያ ማመን ነበር ያቃተን።ሠቆቃ(Torture) በኢትዮጵያ የለም ብለን እናምን ሥለነበር ሥንሰማው ግራ ተጋባን።ጠዋት ሰዬን ሠማኸው ወይ የማታውን ብዬ ጠየቅሁት፣እሱም መስማቱንና ማመን እንዳቃተው፣እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳለ እንደማያውቅ ነገረኝ። “ይህ ነው እንግዲህ የታገላችሁለት”ብዬ እንደቀልድ ጣል አደረግኩ።” ይለናል ብርሀኑ።

ትችት! እሥር ቤት ገብቶ ሳይንገላቱ መፃሕፍት ማንበብና መወያዬት፣ሌሎች እሥረኞችን መቅረብ፣መተዋወቅ፣የተከሰሱባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር መነጋገር፣ከሰዬም ጋር በጥልቀት መወያዬት መቻሉ ፣እሥር ቤቱ ለብርሀኑና ለመስፍን ወልደማርያም የወያኔዎች ኢትዮጵያ እሥር ቤት ሳይሆን የሥካንዲናቪያ እሥር ቤት ሆኖ ታዬኝ።

-ብርሀኑ ከኦሮሞ እሥረኞች መካከል የ80ዓመት ሽማግሌ “አሉኝ” ብሎ የሚነግረን በጣም አሥቂኝ ነው። ወይም ራሱ ብርሀኑ የፈጠረው የፈጠራ ወሬ እንጅ አንድ የ80ዓመት አዛውንት “ግፍ ሥለበዛብን የኢትዮጵያዊነት ሥሜታችን ተሸረሸረ ከማለትም ባሻገር ሥለቅኝ ግዛት ሁኔታም ከአንደበታቸው አይወጣም፣ከወጣም ኦነግ አይደለሁም ያለው የ80ዓመቱ ኦነግ ነው ማለት ነው።ኦነግ ከሆነ ደግሞ “ኢትዮጵያዊ አይደለሁም” ብሎ፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የመጣ ሥለሆነ፣የሚለውን ቢል አድማጩ ብርሀኑና መሰሎቹ ብቻ ሆነው ይቀራሉ።

-ሰዬ አብርሀን በተመለከተ! “ሌባ ሲሰርቅ አይጣላም፣ሲካፈል እንጅ” እንደሚባለው፣ ሰዬ አብርሀ ከመለስ ጋር ትንሽ አለመግባባት ቢፈጥርም፣በዋናው ዓላማ አልተለያዩም። ሰዬም፣ መለስም፣አረጋዊ በርሄም፣ገብሩ አሥራትም ወዘተ፣ሁሉም የትግሬ ዘረኛ ወራሪዎች፣ፀረ-አማራ፣ፀረ-ኢትዮጵያ፣ፀረ-አንድነት እንደሆኑ እየታወቀ ከሰዬ ጋር ብርሀኑ ያደረገው ትርጉም የለሽ ውይይት ምን ይፈይዳል?

በነገራችን ላይ ሥለሰዬ አብርሃ አንድ ልበል።ጎሹ ወልዴ እየተዋጋ ነው በተባለበት ወቅት፣ሰዬ አብርሀ ሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ እንዲህ ሲል አሥደምጦናል፣”ለምን ጎሹ ወልዴ፣ጎሹ ወልዴ ትላላችሁ፣ለእኛ አደገኛው ፕሮፌሰር አሥራት ናቸው።” ያለና አማራውን የገደለና ያሥገደለ፣ኢትዮጵያን ያፈረሰ፣ኤርትራን ያሥገነጠለ ወንጀለኛ ነው። “ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና አንተ ማን እንደሆንክ እነግርሀለሁ” የሚለውን አባባል ብርሀኑ በፀጋ ይቀበለኛል ብዬ አምናለሁ።

-ሌላው የብርሀኑ ትያትር ደግሞ ”ሌሊት የተደበደበ ሠው ጩኸት ሥንሰማ፣ማመን ነበር ያቃተን።ሠቆቃ(Torture) በኢትዮጵያ የለም ብለን እናምን ሥለነበር ሥንሰማው ግራ ተጋባን።ሰዬም ሠምቶ ማመን እንዳቃተው፣እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳለ እንደማያውቅ ነገረኝ” ይለናል ብርሀኑ።”የአይጥ ምሥክሯ ድንቢጥ” እንዲሉ የብርሀኑ ምሥክር ሰዬ ነው።ሰዬ አብሮ ሲሰራው የኖረ የትግሬዎች ወንጀል ሥለሆነ፣ የማያውቀው ነገር የለም። ሌላው አሥገራሚ ነገር ደግሞ ብርሀኑ ሠቆቃ የለም ብሎ ያምን የነበረው፣ በወያኔ ላይ የነበረው የአመለካከት ቅርበት አይምሮውን ደፍኖታል፣አለያም ያሾፋል።ኢትዮጵያ ተወልዶ አድጎ ትምህርቱ አለኝ፣ዕውቀቱ አለኝ ብሎ 24ሠዓት ያለማቋረጥ የሚለፈልፍና ሕዝብን አቅጣጫ የማሳት መሠሪ ችሎታ ያለው ሠው እንዴት ይህ እንደሚሆን አጣው ብለን እንመን? ይህ ሆን ብሎ እንደለመደው “ወያኔን በዲሞክራትነት” ሥሎ፣እንደኖረው ለመቀጠል ሥለፈለገ አውቆ የሚያምታታው እንደሆነ እንገንዘብ።

በነገራችን ላይ ብርሀኑ “የነፃነት ጎህ ሲቀድ” የሚለው መፅሐፉ መታሰቢያነቱ ከተጠቀሱት መካከል” ለሰዬ አብርሃና ለአሰፋ አብርሃ” መሆኑንና በግልፅ ማሥፈሩን ሕዝብ እንዲያውቀው ያሥፈልጋል።

ይህ ሰው ነው ዛሬ በኢትዮጵያ አንድነት ሽፋን ዘረኞችንና ተገንጣዮችን ሥልጣን እንዲያቆናጥጡት እያደራጀ፣ ከወያኔ ጋር ሥልጣን ለመቀራመት በአውሮፓ ህብረትና በአሜሪካ መሥሪያ ቤት ደጃፎች ወጣ ገባ ሲል የሚሥተዋለው።

ምንም እንኳን ወያኔ! ብርሀኑንና መስፍንን የማስመሰል እሥር ቤት አሳይቶ በተግሣፅ ከፈታ በኋላ፣ለሥልጣኑ ማቆያ የይሥሙላ ተቃዋሚ ሥለሚያስፈልገው ቅንጅት እሥከሚመጣ ድረስ “የሚጮህ ውሻ አይናከሥም” እንደሚባለው እያሥጮኸ ሲጠቀምባቸው ቆይቷል።

የቅንጅት አነሳስ እና ውድቀት

ክፍል3

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚገኙ ድርጅቶች ላይ “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ”የሚል የጠነከረ ግፊትና ተፅዕኖ ባቀረበበት ወቅት፣ተባብሮ “ህብረት” ለመፍጠር፣ብዙ ድርጅቶች ከአገር ቤት እነመኢአድ፣ኢዴፓ መድህን፣ የእነመራራ ኦብኮ፣የእነበየነ፣የእነኢዮኤል የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሊግ(ኢዴሊ)፣ከውጭ ደግሞ

እነኢሕአፓ፣መኢሶን፣አረጋዊ በርሄ፣ወዘተ... አሜሪካ አገር ሊሰበሰቡ እንዳቀዱ፣ እነብርሀኑና እነመሥፍን(ፕሮፌሰር) ሲሰሙና ሲረዱ “የእኛ” የሚሉትም የፖለቲካ ድርጅት ስላልነበራቸውና የሕዝቡም “ተባበሩ” የሚለው ግፊት ጣራ ሲነካ ግራ ይጋባሉ።በዚህ ጊዜ እነሱ የሌሉበት ህብረት መፈጠር እንደማይኖርበት በማመናቸው፣በአገር ውስጥ በአገሪቱ ህግ መሠረት ተመዝግበው በምርጫ 97 ሊወዳደሩ ይችላሉ፣ ብዙ አባላትና ተከታይም አላቸው ፣የሚሏቸውን እነመኢአድንና ኢዴፓ-መድህንን መቅረብና ማሳደድ፣ብሎም ወደፊት በቁጥጥራቸው ሥር የሚያደርጉበትን መንገድ ተያያዙት።

በውጭ አገር የሚደረገው የህብረት ስብሰባ የሚደናቀፍበት መንገድ ቢጠፋባቸውም፣ ብዙም ሳይቆይ መኢአድና ኢዴፓ-መድህን፣ ህብረቱ ውሥጥ አለመግባታቸው ታወቀ።ኢዴሊ የሚባለውም እንዲሁ።

ይችን አጋጣሚ በመጠቀም፣ብርሀኑም መሥፍንን በማሳመን ”ቆሎ ይዘህ ከአሻሮ ተጠጋ” እንደሚባለው ወደእነዚህ ድርጅቶች መጠጋት መረጠ።

የብርሀኑ እና የመሰሎቹ ዋናው መሠረታዊ አነሳሳቸውና ህልማቸው መኢአድንና ኢዴፓ-መድህንን ከጊዜ ጋር በቁጥጥር ሥር በማዋል አመራሩን ይዞ ሥልጣን መቆናጠጥ ነበር። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ደረጃውንና ጊዜውን ጠብቆ የሚሠሩ ሥራዎችን እየሠሩ መጓዝ ነው።በመሆኑም የእነብርሀኑ የመጀመሪያ ተግባራቸው የእያንዳንዱን ድርጅት አመራሮች በማግኘትና በማነጋገር ማን ምን እንደሆነ ከተረዱና እነማን ጥንካሬ ኖሯቸው ሊጋፉን ወይም ሊደግፉን ይችላሉ የሚል ሥለላ ያካሂዳሉ።ከአገኙት ግንዛቤ በመነሳት መጀመሪያ በአክብሮት

የቀረቡትና መያዝ አለብን ብለው ያመኑት ከእነዚህ ድርጅቶች በዋናነት ኃይሉን፣ልደቱን፣ግዛቸውን ነበር።

ከእንግዲህ አራቱ ድርጅቶች ቢወያዩም የእነብርሀኑ ሃሳብም ተሰሚነት ሊያገኝ ይችል ይሆናል የሚል ግንዛቤ ለመጨበጥ በቁ።

ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በሚሊዮን አባላትና የሕዝብ ድጋፍ የነበረው በኃይሉ ሻወል የሚመራው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(መኢአድ) ቅድሚያ ቦታ እንደሚይዝ ዓለም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ቀጥሎ ወደ 7 መቶ ሽህ የሚጠጉ አባላት ያለው በእነዶክተር አድማሱና በእነልደቱ የሚመራው የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ መድህን (ኢዴፓ-መድህን) ሲሆን፣ሦሥትኛው ከዚህ ግባ የማይባለው በጣት የሚቆጠር አባላት ያሉት በክፍሉ ታደሰ ተቋቋመ የሚባልለት(በዛሬዎቹ ግንቦቴዎች) በከምባታው ኢዮኤልና በጉራጌው ቸኮል ጌታሁን የሚመራው ኢዴሊ ሲሆን፣ አራተኛው በተወሰኑ ልሂቃን ገና ሳይቋቋም “አለ” በሚል የቀረበ የብርሀኑ፣የአንዳርጋቸውና የመሥፍን ቀስተ ደመና ናቸው።

ቀሥተ ደመና የሚባል እንደድርጅት ሳይፈጠር እነብርሀኑ እንደተፈጠረ አድርገው በመቅረብ የአራት ድርጅቶች አመራሮች(የመኢአድ፣ኢዴፓ-መድህን፣ኢዴሊ እና ቀሥተ ደመና) እያንዳንዳቸው በአራት(4) አራት(4) ሠው እንዲወከሉ የመጀመሪያ ውይይት እንዲያደርጉ፣ እነብልጡ ብርሀኑ በእነአንዳርጋቸው የፅሁፍ ቀማሪነት አጣድፈውና አምታተው፣የመንደርደሪያ ሀሳቦችን ጭምር ይዘው በመቅረብ ውይይት ይደረግበታል። ውይይቱም ብዙ ሳይብላላ ሆን ተብሎ በሩጫና በጥድፊያ(የእነቶሎቶሎ ቤት በመሆን) ወደመስማማት እንዲገፋ ተጣረ ።ይህ ሁሉ ሲሆን ቀስተ ደመና እንደ ድርጅት አለመፈጠሩን የብርሀኑ ፅሁፍ ጭምር ይመሠክራል።

ቅንጅት ሊመሠረት አንድ ቀን ሲቀረው፣እነብርሀኑ በይድረስ በይድረስ፣ተሯሩጠው ቀስተ ዳመና እንደ ድርጅት ተቋቁሞ ራሱን በይፋ እንዲያውጅ ያደርጋሉ።ይህንንም ራሱ ብርሀኑ በፅሁፉ ተናዟል።ከራሳቸው ከቀስተ ደመና መሥራቾች አንደበት የተነገረው ”ቅንጅትን በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት መመሥረት ባይቻል ፣ቀስተ ደመናን መመሥረት አያስፈልግም የሚል” አቋም” ነበራቸው። ብርሀኑ በአሥነበበን ፅሁፉ ደግሞ “አልሸሹም ዘወር አሉ” ዓይነት አገላለፅ በመጠቀም “መመሥረት አያስፈልግም የሚል አዝማሚያ” እንደነበራቸው አልሸሸገም።

እነኚህ ሠዎች ተማምነው የመጡት ከተቻለ ሁለቱን ትልልቅ ድርጅቶች ተጠቅመው ሥልጣን ለመቆናጠጥ፣ካልተቻለ የድርጅቶቹን አመራሮች በተለያዩ ምክንያቶች ገፍትረው፣ የድርጅቶቹን አባላት በቁጥጥር ሥር ለማድረግ እንደነበር ገና ከጅምሩ ያሥታውቅ ነበር።

በማግሥቱ አራቱም ድርጅቶች(መኢአድ፣ኢዴፓ መድህን፣ቀስተ ደመናና ኢዴል) ተሰብስበው የሥራ ድልድል ለማድረግ እኩል በአራት አራት ሠው እንዲወከሉና የበላይ ፖሊሲ አውጭው አካል የላዕላይ ምክር ቤት እንደሆነና የሥራ አሥፈፃሚዎቹን መርጠው “ቅንጅት” የሚል ጥምረት ፈጠሩ።

ከዚህ ቀጥሎ የአመራር ምርጫ ሲያደርጉ፣ኃይሉ ሻወል መኢአድን የመሠለ ግዙፍ ድርጅት ይዞም ሊቀ መንበር ይሁን አይሁን የሚል ክርክር ተነሥቶ “ኃይሉ ግትር ነው፣ነጋዴ እንጅ የፖለቲካ ሠው አይደለም ወዘተ” የሚሉ ክሶች በማቅረብ፣ውጣ ውረድ ውስጥ የሚያሥገባ ድርጊት ውስጥ ለውስጥ በእነብርሀኑ መሠሪነት ቢሞከርም ፣ብዙሀኑ የኃይሉ

ደጋፊ በመሆኑና ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ በመጨረሻ የተሞከረው አሻጥር ከሸፎ፣ በኃይሉ ሊቀመንበርነት ተጠናቀቀ። የሕዝብ ግንኙነቱን ልደቱ እንዲይዝ ተደረገ። ይህ የብልጣ ብልጦቹ የእነብርሀኑ እና የእነአንዳርጋቸው ቀስተ ደመና ብዙ አባላትም ሥላልነበሩት መዳበሉ የነፃ ሎተሪ እንዳገኘ ያህል ነበር።በዚህም ብቻ አላበቃም። የሥራ አሥፈፃሚዎቹ ምርጫ ተደርጎ፣እንደተመረጡና የሥራ ክፍፍል ሲደረግ "ያለምንም ማመንታት በራሴ አነሳሽነት የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴውን እንድመራ ጠይቄ፣የቅንጅቱም ሥራ አሥፈፃሚም ያለማመንታት ተቀበለኝ" ይለናል ብርሀኑ። ከቀሥተ ደመና በፈቃዱ(ዶክተር) የፋይናንስ ኃላፊ እንዲሆን አደረጉ፣አሁን የምርጫ ዘመቻውንና የገንዘቡን ቁልፍ ቦታዎችን ያዙ።
አሁን ቡርቦራውን አንድ ብለው ጀመሩ ማለት ነው።
"ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንዲሉ፣በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አባላት ያሉትን መኢአድን ያህል ድርጅት በአራት ሠው፣ ከ700ሽህ በላይ የሚቆጠሩ አባላት ያሉት ኢዴፓ-መድህንን ድርጅት ከመኢአድ እኩል በአራት ሠው፣ 20 የማይሞላ አባላት ያለው ኢዴሊ ከመኢአድና ኢዴፓ-መድህን እኩል በአራት ሠው እና "ሳይኖር ነበረ" የተባለለት ቀስተ ደመና ከመኢአድን ኢዴፓ-መድህን እኩል በአራት ሠው፣ ማለትም አራቱም ድርጅቶች "እኩል" በአራት፣አራት ሠው ተወክለው ቅንጅት ተቋቋመ ሲባል ፣ገና ከጅምሩ እነመኢአድና ኢዴፓ-መድህን እንዴት በእኩል ቁጥር ሊስማሙ እንደቻሉ፣ለሠሚ ጆሮ ይከብዳል።ቅንጅቱም ውሁድ ድርጅት ሳይሆን የተለያዩት ድርጅቶች የየድርጅቶቻቸውን ህልውናና ነፃነት እንደያዙ በሚጋሯቸው ጉዳዮች ላይ ተቀናጅተው የሚሠሩበት የድርጅቶች ጥምረት እንደሆነ ይታወቃል።
ምናልባትም እነኚህን ድርጅቶች ከእነብርሀኑ ማምታታት በተጨማሪ ያዘናጋቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ብሎ ጠንከር ያል ግፊት ሥላስቀመጠባቸው ይሆን እንዴ ሚዛኑን የዘነጉት? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል።
"በመጨረሻም ቅንጅቱ ከተቋቋመ በኋላ፣የድርጅቱን መሠረታዊ ዶክሜንቶች፣ለመፈራረምና የድርጅቱን ሥራ ለመጀመር የቀስተ ደመና እንደህጋዊ ድርጅት መቋቋም አሥፈላጊ ሥለሆነ ይህንን ሂደት ቀስተ ደመና በአሥቸኳይ ጨርሶ መሥራች ስብሰባው ለጥቅምት 22ቀን 1997ዓ.ም. እንዲጠራ ተወስኖ ስብሰባው ተጠናቀቀ።"
አንባቢ! ልብ በል ቀስተ ደመና የወያኔን "ህጋዊ ዕውቅና" ተብዬውን እንኳን ያሟላው ቅንጅቱ ተፈጥሮ የሥራ ክፍፍል አድርገው ከጨረሱ በኋላ ነበር። እንዲህ ዓይነት "ከፈረሱ ጋሪው የቀደመ የድርጅት አሠራር" ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።
ይህ የቅንጅት መሥራች ሰብሰባ ጥቅምት 22ቀን 1997ዓ.ም. በሩጫና በጥድፊያ ካለቀ በኋላ፣መሥፈርቶቹንና የአሠራር መመሪያወቹን ለመከተል የምርጫው ጊዜ ማጠር ብዙውን ነገር በጥድፊያ መሥራት ግድ ይል ነበር።ከዚያም በቀጥታ የምርጫ ዕጩዎችን ለመመልመል ተጣደፉ።
እዚህ ላይ በቅድሚያ አንባቢ ልብ ሊላቸው የሚገቡ ነገሮችን ላንሳ፣
(ሀ) እንደሚታወቀው ብርሀኑ ቅንጅት ከመቋቋሙ በፊት በእነኢዮኤልና በእነቸኮል ጌታሁን ለሚመራው ኢዴሊ ለተባለው ድርጅት አማካሪ ሆኖ የእነሱ ወረቀት ቤቱ በመገኘቱ ወያኔ ቀደም ሲል "ለ29ቀናት አሠርኩ" ብሎ አሥፈራርቶ ለቆታል። ሥለሆነም ቅንጅት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ሠዎች ብርሀኑ አድርጉ የሚላቸውን የሚያደርጉ፣ የብርሀኑ ታዛዦች እንደሆኑ እንዲታወቅ።
(ለ)ምንም እንኳን የኢዴፓ-መድህን መሪ በተግባር ፀሀፊው ልደቱ እንደሆነ ቢታወቅም፣እንደኃይለማርያም ደሳለኝ ወረቀትና ወንበር የሚያውቀው መሪ ግን አድማሱ ገበየሁ(ዶክተር) ነበር።የኢዴፓ-መድህን ብዙሀኑ አባላት ከአድማሱ ባለቤት ጭምር በልደቱ ሥለሚመሩና አድማሱም ተንሳፎ በመቅረቱ የቅንጅት መቋቋም ለእሱ እንደትልቅ ፈውስ ነበር።በመሆኑም ልክ ቅንጅት እንደተቋቋመ በቀጥታ ለብርሀኑ እጁን በመሥጠት ታማኝነቱን አረጋግጦ፣ብዙውን ጊዜ የሚያጠፋው ኢዴፓ-መድህን ቢሮ ሳይሆን ቀስተደመና ቢሮ ነበር።
(ሐ)ልደቱና መሰሎቹ ደግሞ መኢአድን እንደባላጋራ እንጅ እንደአጋር ባለማየታቸው ይታገሉት ነበር። ብርሀኑም ይህን ሁኔታ ለመጠቀም ሲል ልደቱን ወዳጅ አደረገው።
(መ)ብርሀኑ!የግሉን ዝና ከምንም በላይ ሥለሚፈልገውና ሥለሚሻ፣ በምን ዓይነት መንገድ ተሰሚነት አግኝቶ ቅንጅትን እንደሚቆጣጠረው በማሥላት እና"መኢአድና ኢዴፓ-መድህን ወደፊት መፍረስ አለባቸው" ብሎ መፅሐፉ ላይ ባሰፈረው መሠረት፣አንዱ የሌላውን ሀሳብ እየተቃወመ በቆመ ቁጥር ብርሀኑ እንደአሥታራቂ እየሆነ እየቀረበ፣የእሱ ሀሳብ ፈር እንዲይዝ ማድረጉን ተያያዘው።መኢአድ ሀሳብ ሲሰነዝር ልደቱና መሰሎቹ በእግር በእግር እየተከታተሉ ተቃራኒውን በመሰንዘር መኢአድን ማዳከም፣ኢዴፓ መድህን አንዳንድ ሀሳቦች ሲሰነዝር የእነልደቱ መረን የለቀቀ በመኢአድ ላይ ዘመቻ የሚያበሳጫቸው አንዳንድ የመኢአድ ሠዎች ሁልጊዜም ባይሆን አልፎ አልፎ ተቃራኒውን ይሠነዝሩ ነበር።ይህ"የገበያ

ጋጋታ ለቀጣፊ ጠቀመው" አካሄድ ለብርሀኑ የድርጅቶቹ መቆራቆስ ለእሱ ሎተሪ ነበር።
ብርሀኑ የቅንጅትን የምርጫ ዘመቻ ወክሎ፣ልደቱ ደግሞ የቅንጅትን የሕዝብ ግንኑነት ወክሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በቀጥታ አብረው በመሥራት በሦሥቱ (በወያኔ፣በህብረትና በቅንጅት) መካከል ለሚደረጉት የወደፊት የምርጫ ክርክሮች የቅንጅትን ተከራካሪዎች የመምረጥ ሂደት ውስጥ ገቡ። ብርሀኑም የሚፈልጋቸውን የራሱን ሥድስት(6) ሰዎች ቀድሞ ይዞ ብቅ ይላል፣ልደቱም አማራጭ ይዞ በመቅረብ ያከሽፍበታል።ብርሀኑ እሥካሁን ልደቱን ያቀረበ በመምሰል ድጋፍ እያሰባሰበና እያዘናጋ ቦታውን ይበልጥ ቢያደላድልም፣አሁን ግን የብርሀኑን አካሄድ ልደቱ ለማዬት ዓይኑን ከፈተ። አዲስ ክሥተት ብቅ አለ። ተነቃቅተው እኔ አሸንፍ እኔ አሸንፍ በሚል ግብ ግብ ጀመሩ።
ብርሀኑ ቅንጅትን ሲቀላቀል የተወሰኑ ሰዎችን ይዞ ነበር።አመጣጡም በተቻለው መጠን ሁሉንም በእርሱ መሠሪ አካሄድ ለመቅረፅ በመሆኑ፣ብዙም ሳይቆይ ከመኢአድ ግዛቸውንና መሰሎቹን፣ከኢዴፓ- መድህን አድማሱንና መሰሎቹን ፣ከቀስተ ደመና ከሸመልስ ጭምር፣የእነኢዮኤልና የቸኮል ጌታሁን ኢዴሊ ቀድሞውንም መኢአድንና ኢዴፓ-መድህንን "የአማራ ናቸው" ብለው ሥለሚሸሿቸው በብርሀኑ ተክለ ሰውነት ዙሪያ ያጠነጠነ የውስጥ ቡድን ፈጥሯል። በቅንጅትም
ውስጥ የሚካሄዱትን የውይይቶች ውሳኔዎች ለማሳለፍም፣ላለማሳለፍም፣ለማደናቀፍም ጉልበት እያገኘ መምጣት ጀምሯል።
ምንም እንኳን ትንሽ ቢዘገይም ይህን የብርሀኑ መሠሪ ሥራውን ቀድሞ የነቃበትና በችሎታም በተናጋሪነትም የማይተናነሰው ልደቱ መንገዱ ላይ እንደቆመ ብርሀኑ ተረዳ።ግብ ግባቸው ጦፈ።ከዚያ በኋላ ብርሀኑ ልደቱን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያሳድምበታል፣ድምጥማጡን ለማጥፋትም የውስጥ ለውስጥ ፖለቲካውን ማካሄዱን ያለማቋረጥ ገፋበት።
እንደሚታወቀው ቅንጅቱ ሲመሰረት የእጩ ምልመላ አካሄድን በተመለከተ "አንድ ድርጅት ባለበት ቦታ ሌላው ድርጅት እጩ መመልመል ይችላል፣አይችልም" የሚል ሕግ በቅንጅት ውስጥ ባለመኖሩ ፣ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፣ በድርጅቶቹ መካከል የውስጥ ለውስጥ መራኮትና አለመግባባት ችግርና ፍትጊያ ሥር ሰዶ የቅንጅቱን ህልውና ከመፈታተኑም በላይ፣በመካከላቸው ጠንካራ አሻራውን ጥሎ አልፏል።ነገር ግን ለጊዜውም ቢሆን እየተጠገነና እየተለባበሰ ለእነብርሀኑ ሠርጎ መግባት ዕድሜ የገዛው ቅንጅት፣እንደገና የሡከነ ወይይት በማካሄድ መሠረታዊ ሳይሆን ጊዜያዊ መፍትሄ በመስጠት ቅርበት ፈጥሮ፣እንደምንም ተብሎ "የምርጫ ዕጩዎችን" ለማቅረብ ተችሏል።
ክፍል4
ምርጫውም እሁድ ግንቦት 7ቀን 1997ዓ.ም ተካሄዶ ቅንጅት እንዳሸነፈ ቢታወቅም በማግሥቱ ሰኞ ግንቦት 8ቀን የወያኔ ካድሬዎችና ታጣቂዎች ታዛቢዎችን ጭምር በማባረር የምርጫ ቆጠራ ጣቢያዎችን እንደተቆጣጠሩ፣ ወያኔ «አጠቃላይ ምርጫውን አሸንፈናል እንኳን ደስ ያለን« ብሎ በመገናኛ ብዙሀን አወጀ።የሕዝቡም ቁጣ ጣራ ነካ።
(ሀ)አሁን ብርሀኑ የሄደው የሕዝቡን ቁጣ ለማስተናገድ ወደሕዝቡ ሳይሆን፣ወደነጮቹ ነበር፣ግን ትርፍ አልነበረውም።
(ለ)ይህ በዚህ እንዳለ ቅንጅት ሥብሰባ አድርጎ፣ ከቅንጅቶቹ ኃይሉ ሻወልንና ልደቱን ጨምሮ "ማሸነፋችንን አሥመልክቶ ጠንካራ የአቋም መግለጫ እናውጣ " ሲሉ እነብርሀኑን ደግሞ "እኛ በኢሕአዴግ ላይ ከጠነከርንበት ፣ሕዝቡ በኢሕአዴግ ላይ ካለው ቁጣ ጋር ተዳምሮ፣ የበለጠ ለመናከስ ይነሳል" ይላሉ።ለማንኛውም የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ልደቱ መግለጫውን እንዲያዘጋጀው ቤቱ በተሥማማው መሠረት ተዘጋጅቶ ሲቀርብ፣ሁለት ጠንካራ ዓረፍተ ነገሮች ገብተዋልና ካላወጣህልን ብለው እነብርሀኑ አካኪ ዘራፍ ይላሉ።ልደቱ ግን አልተቀበላቸውም።ሊቀ መንበሩ ኃይሉ አይቶ ሁሉንም ተሰብሳቢ አሥማምቶና አሥተቃቅፎ መሄድን ሥለመረጠ ብቻ፣ሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች እንዲወጡ አሥደረገ።ይህ ልደቱን እንዳሥከፋውና ከሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ብለቅ ይሻላል የሚል ሃሳብ ማቅረብ የጀመረው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነበር።
(ሐ) ይህ በዚህ እንዳለ በከተማይቱ ብዙ ወረቀቶች ይበተናሉ፣ የሕዝቡም ግፊት ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጭምር እየጨመረ ሲመጣ፣ልደቱና መሰሎቹ "ሕዝቡ በራሱ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት እና ትግሉ ከእጃችን ሳይወጣ ቀን ቆርጠን በየከልሉ ሠላማዊ ሠልፍ እንጥራ" ሲል ሃሳብ ያቀርባሉ። ብርሀኑና መሰሎቹ ደግሞ "ይህን እርምጃ ለመውሰድ ድርጅታዊ ዝግጅት የለንም " ይላሉ።ለማንኛውም በልደቱ የሚመራ ኮሚቴ ተቋቋሞ ከተጠና በኋላ "ቅንጅትን ያህል ድርጅት እያለ "ድርጅታዊ ዝግጅት የለንም"፣ ሰልፍ ቢደረግ በቀጥታ ወያኔ ከሥልጣን ሊያወርዱኝ ነው ብሎ የኃይል እርምጃ ይወስድብናል"በሚል ሰበብ እነብርሀኑ ሰላማዊ ሰልፉ እንዳይደረግ ሥለሚፈልጉ የሚያመጡት ምክንያት ከመሆን አይዘልም" ይላል ልደቱ።ያም ሆነ ይህ በብርሀኑና በልደቱ ቡድን መካከል ግብ ግቡ ቀጥሎ ቅንጅቱ የሠላማዊ ሰልፉን አመራር ሳይወስድ ቀረ።
(መ) የተወሰኑ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቅንጅት ቢሮ ድረስ ሄደው ብርሀኑን አግኝተው "ቅንጅት መሪነቱን ወስዶ ሕዝቡን

ማታገል ሥላልቻለ እኛ በቅድሚያ የርሃብ አድማ ለማድረግ አስበናል፣አድማው ውጤት ካላመጣ ወደትምህርት ማቆምና ሠልፍ ሊያደግ እንደሚችል" ይነግሩታል።
በዚህ ጊዜ ብርሀኑ ለቅንጅቱ በወቅቱ አሥታውቆ ቅንጅቱ አመራር እንዲሰጥ ከማድረግ ይልቅ፣የብርሀኑ መልስ "ይህን አድርጉ ወይም አታድርጉ ማለት አልችልም" ብሎ ያሠናብታቸዋል።
(ሠ)ግንቦት 28ቀን ከዩኒቨርሲቲ አንድ ተማሪ ለብርሀኑ ደውሎ "አንድ ነገር አድርጉ፣ እየጨረሱን ነው ቢለውም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎታል።ተማሪዎች እየተጫኑ ወደሰንዳፋ ተወሰዱ፣ግጭት ይፈጠርና አንዲት ወጣት ትሞታለች። የወያኔው ቀኝ እጅ የእንግሊዝ አምባሳደር ለእነብርሀኑ ደውሎ "ይህንን ነገር ማስቆም ባለመቻላችሁ ጥፋቱ የእናንተ ነው" የሚል ቁጣ ይሠነዝራል።ብርሀኑ በልምምጥ የመለሰው መልስ "ቅንጅት እንደሌለበትና እንዲህ ዓይነቱን እንደማይደግፈው" ነው። ያም ሆነ ይህ የእንግሊዙ ወያኔያዊ አምባሳደር ሕዝቡ ያለቅንጅት አመራር በራሱ ተነሳሽነት ያደረገው መሆኑን ከራሱ ሠላዮች መረጃ አገኘ።።
(ረ)በሰኔ 30ቀን ውጥረቱ ነግሶ፣አጠቃላይ የሥራ ማቆም አድማ የሚጠራ ወረቀት ተበተነ። ወረቀቱ እነ ብርሀኑ እጅ ሲገባ ነብስ ውጭ ነብስ ግቢ የሆነ ሁኔታ ይፈጠርና ቅንጅቱ በሁለት ጎራ ይሠለፋል። አንደኛው "እኛ (የቅንጅት አመራሮች) የሕዝቡን ትግል መምራት ካልቻልን ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት የሚያደርገውን ትግል መደገፍ፣ወይ ዝም ማለት ነው ያለብን መቃወም ግን የለብንም" የሚል ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ "በአውሮጳ ኅብረት አደራዳሪዎች በኩል ውይይት ሊደረግ ነውና ይህ የሥራ ማቆም አድማ እንዳይደረግ መሞከር አለበት" በሚል እነብርሀኑ መግለጫ አውጥተው በራዲዮና በቴሌቪዥን እንዲነገር ይላካል፡፤ወያኔ ግን አላስተላለፈውም። በዚህ ጊዜ ብርሀኑ "ችግር" ብሎ የሚጠራውን የሕዝቡን የሥራ ማቆም አድማ እንዳይደረግ ለመከላከል ቢፈልግም፣ ሊከላከለው ባለመቻሉ ከፍተኛ ፍርሀትና ጥርጣሬ ሥላደረበት የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮን በመቅረብ፣ ከሕዝብ አድማ በተቃራኒ በመቆም ቅንጅት የሥራ ማቆም አድማ እንዳልጠራ ቃለ መጠይቅ አደረገ፣ ግን በማግሥቱ የሚደረገውን የሥራ ማቆም አድማ ሊያስቆመው አልቻለም።
-ብርሀኑ!በሰኔ 1ቀን በተጠራው የሥራ ማቆም አድማ ምክንያት ማታውኑ ሰኔ 30ቀን "እርምጃ ይወስድብኛል" በሚል ፍርሀት ቤቱን ለቆ ከሚስቱ ጋር አና ጎመዝ ያረፈችበት ቦታ ሸራቶን ሆቴል ሄዶ አደረ።
(ሰ)ወያኔ! ምርጫው ሳያልቅና ሳይጠናቀቅ ቀድሞ በራዲዮም፣በቴሌቪዥንም ሆነ በጋዜጣ "አሸንፌአለሁ" ብሎ ለዓለም አሥታውቋል፣በአራት ነጥብ ደምድሟል።ከዚህ ነቅነቅ እንደማይል የወያኔ ምንነት ለብዙ ዓመታት ይታወቃል። የነጩ ዓለምም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ሳይሆን ከወያኔ ጎን ተሰልፎ፣ወያኔን በ1983ዓም ሥልጣን ላይ አሥቀምጦ ሲያስጨፍርብን እንደኖረ  የምናውቀው ሀቅ ነው።በዚህም ጊዜ ነጮቹ ማስመሰሉን ሥለሚያውቁበት፣ የሰኔ አንዱ ግድያ ከመፈፀሙ በፊት" የምርጫ ችግር ለመፍታት" በሚል ሦሥቱ አካሎች የአውሮፓ ህብረት አምባሳደሮች እና የአሜሪካ አምባሳደር በጋራ የጀመሩት ወገናዊ ወያኔያዊ የማዘናጋትና የጊዜ መግደያ ውይይት ተብዬው ብቅ አለ።ነጮቹ ዕውነትን ቢመርጡ ኖሮ ወያኔ ሳያሸንፍ አሸንፌአለሁ ባለበት ወቅት፣"ምርጫው ሳይጠናቀቅ ማሸነፍና መሸነፍ ሊታወቅ አይችልም፣ሥህተት ነው "ብለው መገሰፅ በቻሉ ነበር።ነጬ ውይይት የሚለውን የያዘው ገንፍሎ የተነሳው ሕዝብ ወያኔን እንዳይጥል፣በአንፃሩ ወያኔ የሚያስረውን እያሠረ የሚገለውን እየገደለ ማሥደንገጡን ቀጥሎ ሥልጣኑን እንዲያጠናክር ካላቸው ፍላጎት በመነሳት ነው።ምክንያቱም በዚያ አካባቢ የእነሱን ፍላጎትና የቁጥጥር ጥቅም ሊያስጠብቅላቸው የሚችለው ወያኔ ብቻ ነው ብለው ሥላመኑ።
ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰውም፣ቅንጅት ተፈጥሮ ምርጫ ዘመቻ ውስጥ የገባው በአጭር ጊዜ ነበር።ብዙውን ሥራም ለማከናወን ይበልጥ በይድረስ በይድረስ ቢጀመርምና ምርጫ ቢያከናውንም ፣ብርሀኑና መሰሎቹ መድረኩን ሥለተቆጣጠሩት፣እግረ መንገዳቸውን በመኢአድና በኢዴፓ-መድህን ላይ የሚያደርጉትን ቡርቦራና ማዳከም ሳይዘነጉ፣ቅንጅት በጀመረው ጥንካሬው እንዳይቀጥል፣ለወያኔ ተንበርካኪ እንዲሆን፣ ሰላማዊ ሰልፍንም በመከላከልና ወያኔ እንዳይወድቅባቸው የወያኔን ሥልጣን ለማቆዬት በሚራወጡት ነጮች ላይ ተጠመዱ።
ሕዝቡም ያለመሪ በአደባባይ ወጥቶ ከመሞቱና ከመደብደቡ በፊት "እንዴት አሥተባብረን እንምራው" ከማለት ይልቅ ከወያኔ ሠዎችና ነጮች ጋር የይሥሙላ ድርድር ተብዬው ውስጥ መዋኘቱ የወያኔን ምንነት ለተረዳ፣አደጋ እንዳለውና ውጤተ ቢስ እንደሆነ ቀድሞ ይታወቅ ነበር።
ያም ሆነ ይህ በወያኔ ያለቀለትን "የምርጫ ሂደት ውይይት"ተብዬው ፣ብርሀኑ ሰኔ 1ቀን ከበረከት ሥምዖን ጋር ለመደራደር በሚል ሰበብ ወደ በረከት በሄደበት ዕለት አድማው ተግባራዊ ሆነ። ብርሀኑም በወያኔ ወታደሮች ብዙ ሕዝብ ማለቁን ሠማ፣አሁንም ምንም ሳያደርግ በረከትን ይጠብቃል፣ ግን በረከት የለም።

ቅንጅት በ97 ምርጫ ለመግባት ሲወስን ኢህአዴግ የሚያስቀምጣቸው ጋሬጣዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አውቆ፣ብቸኛው አማራጭ በምርጫ ምክንያት የሚገኘውን ቀዳዳ በመጠቀም ማህበረሰቡን ማንቃትና የወያኔን የጭቆና ቀንበር ከላዩ ላይ ለማውረድ በጉልበት አልገዛም የሚል ሥነ-ልቦናዊ ጥንካሬ ለማጎናፀፍና ለነፃነቱ ጥብቅና ብቁ እንዲሆን ነው። ታዲያ ህዝቡ ሙብቴ ይከበር ብሎ ሲነሳና ያለመሪ ሲያልቅ ከወያኔ ጋር ድርድር ምን ይባላል?

አሁን ወያኔን በሚመለከት ቅንጅት በሚሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በተለሳለሰ አቋም በሚያምነው ብርሀኑና በወቅቱ ጠንካራ አቋም ይዞ በነበረው ልደቱ ቡድኖች መካከል ትልቅ ልዩነት ተንፀባረቀ።

የምርጫ ማጣራቱን ሂደት በምርጫ ቦርዱ ወሳኝነት ሲካሄድ ሂደቱን እንደሚያበላሸውና በመጨረሻም ቅንጅቱን ወደነበረበት ቦታ እንደሚመልሰው በቅድሚያ ይታወቃል።ሆኖም ግን "የማጣራት ሂደቱን የምርጫ ቦር ያካሂዳል፣ይህንን ብትፈልጉ ተቀበሉ ባትፈልጉ ተውት" ሲል የወያኔው መለስ፣ነጮቹም ሆኑ ብርሀኑ ተሥማምተው ሄዱ።

ከዚህ ቀጥሎ ብርሀኑ የድርድር ፅሁፍ አቅርቦ "ቅድመ ሁኔታ በሚል ያሰፈራችሁት ሥህተት መሆኑን ካልተቀበላችሁ ድርድሩ ፈርሷል"ብሎ በረከት ይቧርቃል። ነጭ አምላኪው ብርሀኑ! "ቅድመ ሁኔታ" ከተባለው ነፃ ነው ብሎ ያመነበትን በእንግሊዝኛ አዘጋጅቶ ለአደራዳሪ ተብዬው ለነጩ ለቲም ክላርክ ልኮ እንዲያፀድቅለት ካደረገ በኋላ፣ በቅንጅት ሳይሆን በቀሥተደመና ድረ-ገፅ ላይ ለጠፈው።እንደገና ከእነበረከት ጋር ስብሰባ ሲደረግ አሁንም" ቅድመ ሁኔታው"አልተነሳም በማለት እነበረከት ውድቅ አድርገው የራሳቸውን እንደሚከተለው አቀረቡ። "በቅንጅት በኩል ቅድመ ሁኔታ በሚል የቀረበው ሥህተት" መሆኑን በመግለፅና "ይህ እንቅፋት በመነሳቱ የማጣራት ሂደቱ ሥምምነት መስመር እንደያዘ" በረከት ይገልፃል።

በዚህ እነበረከት ባሉበት ስብሰባ ላይ ነው ቲም ክላርክ "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" ዓይነት አሰራር በመጠቀም፣ብርሀኑና መራራን ለአውሮፓ ፓርላማ አቋማቸውን እንዲያቀርቡ የጋበዛቸው።መራራ ሥላልቻለ ነገደ ጎበዜ ሊወክለው በቅቷል። ይህንን ነጩ በውስጥ ለውስጥ ከወያኔ ጋር ተነጋግሮ ለማስመሰልና ለጊዜ መግዣ ነው ወይስ ለምን? ምርምሩን ለአንባቢ እተወዋለሁ።

ቀኝም ነፈሰ ግራ የቀረቡትን 10ነጥቦች በረከት ውድቅ ሲያደርጋቸው፣አደራዳሪውና ዲፕሎማቶቹ ነጮች ከወያኔው መለስ ጋር እጅና ጓንት ሥለሆኑ፣እንደአማላጅ መሥለው ለመለስ ነግረው "10ነጥቦች ተቀብያለሁ" ቢልም በምርጫ ቦርዱ አማካይነት አንድ በአንድ ውድቅ እንደሚሆኑ አውቆ ነበር።እናም ውድቅ ሆኑ። ወያኔን እንዳያሥቀይሙ እየተባሉ የተለሳለሱ ፅሁፎች እየተዘጋጁ ከልምምጥ ጋር ቢቀርቡም ሁሉም ውጤት ቢስ ሆኑ።

ይህ የሆነው በሕዝቡ ላይ ግድያና እሥር ከተካሄደበት ሰኔ አንድ(1) 1997ዓ.ም. ማግሥት ጀምሮ ነበር።በዚህ በሕዝቡ ሠላማዊ የተቃውሞ ወቅት በአካባቢው ያልነበሩ ብዙ የቅንጅቱ አባሎችም እንደአውሬ እየታደኑ የሚታሰሩበት ጊዜ ነው።ቅንጅት ቢሮ የሚሠሩ የቀጠና አሥተባባሪዎችም ታሥረዋል።በየክልል የሚገኙ አደራጆች እየተሳደዱና እየታሰሩ ነው።በአመራር አካላቱም ላይ ወከባው ጣራ ነክቷል።በዚህን ጊዜ በኢንጂንዬር ኃይሉና በልደቱ ላይ የሚደርሰው ክትትል ጠንክሮ ሁለቱም በዕቁም እሥር ላይ ነበሩ።

አሁን ብርሀኑ ወደአውሮፓ ሊሄድ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ከአገር እንደማይወጣ ይከለከላል።ወዲያው ለነጩ ለቲም ክላርክ ደውሎ መከልከሉን ከተናገረ ከ20 ደቂቃ በኋላ እንዲወጣ ተፈቀደለት።ውጭ ወጥቶ የአውሮፓ ፓርላማን፣በየአገሩ ያሉትን የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሮችን፣የቅንጅት ደጋፊዎችንና በገንዘብ አሰባሰቦችም ላይ ተካፍሎና የግል ደጋፊውን አበራክቶ ወደኢትዮጵያ ገባ።ዛሬ በብርሀኑ በኩል የገጠመን ችግር ከዚያ ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ልደቱ በምርጫ ቦርድ የተያዘውን የማጣራት ሂደት ድርድር በመቃወም "ቅንጅቱ የተፈራረመው የምርጫ ማጣራት ሂደት ስምምነት እንደ አልጀርሱ ሥምምነት አገርን ወይም የሕዝቡ ድምፅ ይከበር የሚለውን የሕዝብ ጥያቄ መካድ ነው" የሚል መግለጫ ሠጠ።

ብርሀኑም ብዙም ሳይቆይ "የምርጫ ማጣራት ሂደቱ በተጀመረ በሦሥተኛው ሳምንት ገደማ ከንቱና ክሽፍ በመሆኑ ፣ራሳችንን ያገኘነው ከማጣራት ሂደቱ በፊት የነበርንበት ሁኔታ ላይ ነው" ብሎን አረፈው።

ብርሀኑ! ሕዝብን አሥተባብሮ ከመምራት ይልቅ፣በቅንጅት ውስጥ በፈጠረው ቡድን በመመካት ሩጫውን ለፋይዳቢስ ድርድር ወደበረከት፣ወደመለስ፣ወደነጮቹ፣ወደወያኔው ምርጫ ቦርድ፣ወደአውሮፓ ህብረት መሯሯጥን መረጠ።

ከምርጫ ማጣራቱ ሂደት መክሸፍ በኋላ መረጋጋት ለመፍጠር በሚል ፈሊጥ ነጮች ከራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም በመነሳት ቅንጅት ፓርላማ እንዲገባ ግፊት ማድረግ ጀመሩ።

አሁን የድርድር አጀንዳዎች አንድ በአንድ ውድቅ ሆነዋል።በዚህ ጊዜ "የወያኔው ሪፖርተር ጋዜጣ አዘጋጅ አማረ አረጋዊ

ኢሕአዴግ የኃይል እርምጃ የማይወስደውና ሠላምም የሚያመጣው፣ "የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ቢቋቋም ነው"በማለት ጋዜጣው ላይ ያወጣውን ሀሳብ፣ ብርሀኑ ደግፎ ለመደራደሪያ ሊጠቀምበት ተነሳ ።ይህ የህብረቱም አቋም ነበር።የህብረቱ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ጥያቄ ለአገሪቱ የወያኔን ህገ-መንግሥት ሽሮ ሌላ ሕገ- መንግሥት ማውጣት የሚል ሲሆን፣የብርሀኑ ቅንጅት የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ጥያቄ ደግሞ "የወያኔው ፓርላማ፣ፍርድቤቱ፣ምርጫ ቦርድ፣ደህንነት ወዘተ" ፍፁም ነፃና በወያኔ ሕገ-መንግሥት መሠረት እንዲሠሩ ማድረግ ነው"ብሎ ይነሳል። ብርሀኑ! "የወያኔ ህገ መንግሥት ይቀዬር" የሚለውን ሃሳብ ህብረቱ ለጊዜው እንዲያቆዬው ተማፅኖ ፅሁፍ ፃፈ። በዘር በተቋቋሙ ሰዎች በእነበዬነና በእነመራራ የሚመራው ህብረት የወያኔው ሕገ መንግሥት እንዲቀየር ቀርፆ ሲሟገት፣ቅንጅትን ወክያለሁ የሚለን ብርሀኑ ግን አገርና ሕዝብ አጥፊ በሆነው በወያኔ ሕገ መንግሥት ሥር መተዳደርን መምረጥ የሚያሳዬን ብርሀኑ ገና ከመነሻው ለወያኔ ጠቃሚ አቋም ይዞ ይጓዝ እንደነበር ነው።

ለማንኛውም ፅሁፉ ወደመለስ ተላከ። ከመለስም የተገኘው ውጤት እነብርሀኑን አራክሶ፣አዋርዶና አሥፈራርቶ መመለስ ነበር።

ክፍል5

ልብ በሉ! ወያኔ ቀደም ሲል ምርጫውን አሸነፍኩ አለ፣ቀጥሎ የምርጫ ስምምነት ሂደት በሚል እነብርሀኑ ያቀረቡትንም አከሸፈ።አሁን ደግሞ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ጥያቄም ውድቅ ሆነ።

ከዚህ በኋላ ቅንጅት ሕዝቡን ለሥብሠባ ጠራ።

(1) ሕዝቡ! "ወያኔ የሚገባውና የሚሰማው ብቸኛ ቋንቋ ሕዝቡን ለሰላማዊ ትግል ማንቀሳቀስ እንጅ ከእሱ ጋር የሚደረግ ድርድር መፍትሄ አያመጣም" ሲል ፣ብርሀኑ ደግሞ "ለኢህአዴግ የጥላቻ ፖለቲካ፣ መልሳችን መሆን ያለበት ፍቅር ነው" በማለት ወያኔን አትንኩብኝ ንግግር አደረገ።

(2) ሕዝቡ! "ለወያኔ የቀረቡት ጥያቄዎች ሥላልተመለሱ ፓርላማ ልትገቡ አትችሉም" ሲል፣ ብርሀኑ ፓርላማን አሥመልክቶ የሄደበት ዙሪያ ጥምጥም መንገድ ደግሞ "ዋናው ጥያቄ የፓርላማ መግባት አለመግባት ሳይሆን የዲሞክራሲያዊ ሂደቱን ያግዘዋል ወይስ አያግዘውም የሚል መሆን አለበት"ይላል። (3) ሕዝቡ!"ፓርላማ አትግቡ" የሚለውን አሥረግጦ በመናገር ይደመድማል።በዚህ ጊዜ ብርሀኑ የሕዝቡ አቋም እንደማይነቃነቅ ሲረዳ፣ቀጠል አድርጎ ሕዝቡን እንዲህ ሲል ይጠይቃል "የእናንተን ሠምተናል የመግባትና ያለምግባትን በተመለከተ እኛ አመራሮቹ ሁኔታውን ዓይተን አንዱን ብንመርጥ ትቀበሉናላችሁ? ታምኑናላችሁ ወይ?"ሲል ይጠይቃል።የተወሰነው ሲያቅማማ፣የተወሰነው"አዎን" ይላል።ይችን ለምን ጠየቃት።መልሱን ወደፊት የምናዬው ይሆናል።

አሁን ብርሀኑ! ምርጫውም ሆነ ድርድሩ ብሎም የቤት ውስጥ ስብሰባው በወያኔ ጉልበተኝነት እንዳለቀለትና እንዳከተመ ካረጋገጠ በኋላ፣

አራቱ ድርጅቶች በተለይ ለማፍረስ የዛተባቸው መኢአድና ኢዴፓ-መድህን ሳይቀሩ በየድርጅቶቻቸው ከቆሙ ባዶውን እንደሚቀር ሥለተረዳው፣ባሥቸኳይ ወደውህደት መሮጥ ጀመረ።

እንደሚታወቀው

(1ኛ)የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅቶችን "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ሥላላቸው ብቻ ይመስላል፣ሳይጠናኑ፣በይድረስ በይድረስ የጥድፊያ ጥምረት ፈጠሩ። (2ኛ)ቅንጅት ገና ከጅምሩ ጀምሮ የድርጅቶች ጥምረት ወይም ህብረት እንጅ እሥከዚህ ጊዜ ድረስ የተዋሀደ አንድ ፓርቲ አይደለም።

(3ኛ)በውጭም በውስጥም የነበረው ብዙሀኑ ደጋፊ ሕዝብ ከልቡ ድጋፉን ለቅንጅት ሲሰጥ፣የማያውቀው ነገር ቢኖር ድርጅቶቹ ተቀናጅተው ሲሰሩ፣ ገና ከጅምሩ ጀምሮ የማይስማሙና ሽኩቻ የበዛባቸው እንደነበሩ ነው።

(4ኛ)ቅንጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንሥቶ ለውህደት የሚያበቃ ዕድሜ አልነበረውም።የአራቱም ድርጅቶች አባላት የረጅም ጊዜ ሥር የሰደደ ትውውቅ አልነበራቸውም።

እነኚህ አራት ድርጅቶች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ፣በውስጣቸው የነበረውን መናቆርና አለመተማመንን ሳያስወግዱ፣ ከዚያም በላይ በዚህ አካሄድ የሚመጣ ውጤት "ከድቡሽት ላይ የተሠራ ቤት" እንደሚሆን ከወዲሁ ቀድሞ ይታወቅ ነበር። ብርሀኑ! ይህን ከፈረሱ ጋሪው የቀደመ ውህደት ለመፈፀም በሚል ከፕሮግራም በተጨማሪ፣ባለ50ገፅ የመተዳደሪያ ደንብ ፅሁፍ አንዳርጋቸው ፅጌ አዘጋጅቶ የቅንጅት ሳይሆን፣ የቀስተ ደመና አመራር አፅድቆት፣ በራሱ ድርጅት በቀስተደመና ድረገፅ እንዲወጣና የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች እዚያ ገብተው እንዲያዩት ይነገራቸዋል።ይህንንና ይህንን መሰል የእነብርሀኑ አካሄድ ትልልቆቹን ድርጅቶች ወደጎን የመግፋት አባዜ እየጎላና እየጠነከረ መምጣቱን ልብ ይሏል።

መኢአድ ኢንጂኔር ኃይሉ! (1)በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በቀጠና የአደረጃጀት መዋቅር መሄድ በደንብ እንደጠቀማቸውና ከመኢአድ ልምድ ሌሎቹም እንዲቀስሙ ቢታገልም እነብርሀኑ ተቃራኒውን መረጡ።
(2)ሌላው የመኢአድ ተቃውሞው በሽግግር ድንጋጌው ላይ ነበር።ይኸውም አመራሩ አሁንም ከአራቱ ድርጅቶች የተውጣጣ መሆን እንዳለበትና የአመራር ምርጫው ቀመር ደግሞ ፓርቲዎችን እንደጥንካሬያቸው (በአባላት ብዛት፣በፋይናንስ አቅም፣በተግባር ልምድ ወዘተ) ማበላለጥ አለበት የሚለው ሀሳብ ለምን ተቀየረ? ብሎ የውህደት ኮሚቴውን ወጥሮ ያዘ።ሁሉም ድርጅቶች ከላዕላይ ምክር ቤት አባላት ብዛትም ሆነ ድርጅታዊ ሥብጥር ጀምሮ እኩል መሆን አለበት በሚል ነው የቀየርነው" ይላል ብርሀኑ ።መኢአድም "ብዛታችንም፣የድርጅት ጥንካሪያችንም የታወቀ ነው፣ይህ ችግር ሊፈጥር አይገባም "ይላል። በዚህ ጊዜ ልደቱ የመኢአድ ነገር ሲነሳ ቀንዱ ሥለሚቆም እንዲህ ይላል"ኢዴፓ-መድህን የእኩልነትን መርህ ያምንበታል፣ይቀበለዋልም" ይላል።ይህ ለመኢአድ ችግር ፈጠረ።ብርሀኑም ሲሰራው የኖረው ሻጥር ፍሬ አፈራለት። መኢአዶችም የእኩልነት መርህን አንቀበልም ካሉ ሌሎቹን ትናንሽ ፓርቲዎች (ቀስተደመናንና ኢዴሊን)እናስቀይማለን ብለው ሠጉ"። በመሠረቱ ከሌሎቹ የላቀ ድርጅት ይዘው ከሌሎቹ ትናንሽ ፓርቲዎች እኩል መወከሉ ትክክል አልነበረም።"ከ150 በላይ የሚሆኑ ላስቀራቸው የማልችለው የየዞኑ ተጠሪዎችና የማዕከላዊ ኮሚቴው አባሎች አሉኝ" ብሎ መኢአድ አቀረበ።ሁኔታውን ገምግመውና እና የሚገጥመንን ችግር ተረድተው ቢቻል ትንሽ ተጨማሪ ሰዎች ለአመራር ቢሰጠን ብለው ጠየቁ ግን ሰሚ የለም።
በመኢአድ ላይ ሲደረግ የነበረው ጫና መረን የለቀቀ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት ከምንም በላይ ሆኖ ሥለታያቸው የፈለገውን ያህል ጫና ቢደረግባቸውም እና ብዙ አባሎቻቸው ቢገፉም ትልቁን ጉዳይ ተግባራዊ ለማድረግ ከልብ መቀጠል መረጡ።እነብርሀኑም አጭበረበሩ፣እነልደቱም ተንጠራሩ ፣የኢንጂኔር ኃይሉ ዋናና ብቸኛ ፍላጎት የኢትዮጵያ ሕዝብ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚል ጫና ማስቀመጡን ግንዛቤ ውስጥ ከማስገባቱም ባሻገር ፣የኢትዮጵያን አንድነት ተግባራዊ ሆኖ ማዬት በመሆኑ ሁሉንም ነገር ለአንድነት ሲባል "ይሁን" እያለ ይቀበል እንደነበር ይታወቃል።
አሁን ኢዴፓ-መድህን በልደቱ አመራር ፀረ መኢአድ አቋሙ ጣራ ነክቷል፣ብርሀኑና ልደቱም ከተነቃቁ ውለው አድረዋል፣ ብርሀኑ ቀስተደመናና ኢዴሊን እንዲሁም እነኢንጂነር ግዛቸውን፣እነዶክተር አድማሱን በመያዝ ቅራኔዎቹንም በመጠቀም ትልቅ ተዓምር ሊሠራ ነው።
እንደሚታወቀው ብርሀኑ ለአዲስ አበባ ከንቲባ ምርጫ ሥለተመረጠ በውህደቱ አመራር ሊገባ እንደማይችል ቀድሞ ያውቀዋል ፣ግን ከቀስተደመናና ኢዴሊ የሚፈልጋቸው ሠዎች በአመራር መግባት እንዳለባቸው አቅዷል። ገመድ ጉተታውና ውጣ ውረዱ ተጧጡፎ የፈለገው ምክንያት ቢደረደርም ኢንጂነር ኃይሉ አሁንም ሊቀመንበር ሆኖ ተመረጠ።በአሁኑ ጊዜ የኢንጂነር ኃይሉ ለውህደቱ መመረጥ ብርሀኑን ብዙም አልረበሸውም ምክንያቶቹም (1) የሕዝብ ድጋፍ ሥላለውና ከብርሀኑ አቅም በላይ ሥለሆነበት፣(2)ኃይሉም በህመም ምክንያት አመራሩን በአጭር ጊዜ ይለቃል ከሚል እሳቤ፣ (3)"ኢንጂነር!አመራሩን እንደያዘ ቢቀጥልም ከእርሱ ጋር የሚመሩት ሠዎች የእኔ(የብርሀኑ) ሠዎች መሆን ሥላለባቸውና በእነሱ አማካይነትም ቀጣዩን ሥራዬን ለመሥራት እችላለሁ"ብሎ በቅድሚያ ተዘጋጅቷል።
ከዚህ ቀጥሎ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር መሆን የሚገባው ከሁለተኛው ፓርቲ ኢዴፓ-መድህን ነበር። እነብርሀኑና እነአድማሱ የፈለጉት ዶክተር ኃይሉ አርአያን ነበር። ነገር ግን ይህን
ሠው ኢዴፓ-መድህን አልመረጠውም።ሥለዚህ የራሱ ድርጅት ያልመረጠው ሠው ቅንጅት ውስጥ ሊመረጥ አይችልም።ድርጅቱ ኢዴፓ-መድህን መርጦ ያቀረበው እጩ ልደቱ ነበር።ድርጅቱ መርጦ ከላከው ተወደደም ተጠላም ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር መሆን የሚገባው የኢዴፓ መድህን ሠው ነው ከተባለ ልደቱ መሆን ነበረበት።
ብርሀኑም ቀድሞ በሠራው የቤት ሥራ መሠረት ልደቱን ገፍትሮ በግርግር ተሯሩጦ ብርቱካንን አሥመረጠ።ፀሀፊም ከምክትል ሊቀመንበር በኋላ ሥለሚመረጥ ፀሀፊነቱን ልደቱ እንዳይዝ በማሰብ" ይላል ብርሀኑ፣እንደ ድርጅት ኢዴፓ-መድህንም አንድ ቦታ መያዝ ሥላለበትና ያም ቦታ ዞሮ ዞሮ በልደቱ ሥለሚያዝ፣ልደቱ ተመርጦ ሥልጣን የለሽ ሽባ የሚሆንበት ቦታ ምክትልነት ብቻ ነው በሚል"ልደቱን ምክትል ሊቀመንበር እንዲሆንና የኢዴፓ-መድህንን ቦታ እንዲሞላ አደረግነው። የፀሀፊነቱ ቦታ ለኢዴሊ ኢዮኤል ተሰጠ" ይላል ብርሀኑ።አሁን ብርሀኑ ቁልፍ ቦታዎችን በራሱ ሠዎች አሥይዟል።
ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርነቱን ከኢዴፓ-መድህን አንሥቶ ለቀስተ ደመና መሠጠቱ ያቃጠለውና ያናደደው ልደቱ፣"ምክትል ነህ" ቢሉትም ከምንም አልቆጠረውም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ "ቆይ አሳያችኋለሁ" በማለት በእርግጠንነት

ጦርነት እንደጀመረ ይነገራል።

ይህ በዚህ እንዳለ ሊቀ መንበሩ ኢንጂኔር ኃይሉ ብዙ ጊዜ ሥለሚያመው ውህደቱ ሳይገባደድ፣ለህክምና ወደውጭ በሄደበት ወቅት መሰሪው ብርሀኑ ቅንጅትን በመዳፉ ለማስገባት እንደውሁድ ፓርቲ በይድረስ በይድረስ ካምታታ በኋላ ባቀደው መሠረት መሥከረም 14ቀን "ውህደት"ተብዬውን አጣድፎ፣ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበሯ የውህደት ንግግር "ቅንጅት መንፈስ ነው" ብላ እንድታደርግ ያደርጋል።ብርሀኑም "መኢአድም፣ኢዴፓ-መድህንም ሞተዋል፣ከአሁን ጀምሮ የቅንጅት ውሁድ ፓርቲ" ነው ያለው" በማለትና በመቋመጥ፣በምርጫ ቦርድ ለማስመዝገብና ቦታውን ለማደላደል ይጥራል።በሌላ በኩል በአራቱ አመራሮች በኩል የሥራ አሥፈፃሚ አባላት የሥራ ምደባ ጎን ለጎን እንዲሄድ ይፈለጋል።

በዚህ ጊዜ ልደቱ የኢዴፓ-መድህን ሦዎች ተገፍተዋል፣የሚገባቸውን ቦታ አላገኙም ብሎ ያነሳል።ከዚህ ተከትሎ እነብርሀኑ ልደቱን "የአራቱ ድርጅቶች መሪዎች ፈርመዋል ሦሥት ማህተም ተደርጓል የእናንተ ማህተም ነው የቀረውና ማህተም አምጣ" ይለዋል።ልደቱም "ማህተም አልሰጥም ካለ በኋላ ቀጠል አድርጎ "ውህደቱም መዋቅሩም አሁኑኑ በጥድፊያ ካልተሠራ የምትሉት ግልፅ ያልሆነ የበሥተጀርባ ተንኮል ያላችሁ ናችሁ፣ የቅንጅትም ህጋዊ ዕውቅና እሥከ ምርጫው ማለቂያ ድረስ እንደሆነ ሥለሚታወቅና አሁን ምርጫው ሥላበቃ፣እንደ እሥከዛሬው የየድርጅቶቻችንን ህልውና እንደያዝን ሆነን፣የእሥከዛሬውን አካሄድ በቀጣይነት ለመሥራት የነበረውን ቅንጅትን ለማስቀጠል ፈቃድ ማግኘት ብቻ ነው መፍትሄው።ውህደት የምትሉት አይሠራም ኢዴፓ-መድህንንም አይመለከትም"ይላል።ይህንን ከተቀበላችሁና በዚያ ላይ ጥረት የምናደርግ ከሆነ እሠየው፣አለበለዚያ የማትቀበሉ ከሆነ በየድርጅቶቻችን ሥራችንን እንሥራ።እኛም በራሳችን መንገድ እንሄዳለን" ይላል። ማህተምን በተመለከተ እነዶክተር አድማሱ አዲስ ማህተም አሠርተው፣የቅንጅቱን ውህደት ለማስመዝገብ ቢሞከርም ወያኔ አልፈቀደም።

ልደቱን በሚመለከት መዐሕድ በነበረበት ወቅት ሥራ ለመቀጠር የሥራ ማሥታወቂያ አይቶ ሲያመለክት ሁለት የመዐሕድ አመራሮች የድጋፍ ደብዳቤ እንደፃፉለት ይታወቃል።ሲቀጠር የማያውቀው፣ለጥቂት ወራት እንደሠራ "በደህንነት ሥራ" እንዲቀላቀላቸው ድህንነቶች ይቀርቡታል። "አልሞክረውም፣አላደርገውም" ብሎ ሥራውን ጥሎ መውጣቱ ይታወቃል።ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ "ልደቱ ለደህንነት ተመልምሎ ነበር"እያሉ አሉባልታ መንዛት ለራስም አመኔታን ያሳጣል፣ለአገርም ጎጅ ነው።ሠራው የተባለውን፣ማሥረጃ የማይቀርብበትን ከዕውነት የራቀ አሉባልታን በመደጋገም የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል እንደ ዕውነት አድርጎ ማቅረብ የግለሰቡን ሥብዕና ከማርከስም በላይ ወንጀል ነው።አሉባልታ በሚያናፍሱትም ቡድኖች ላይ ሕዝብ አመኔታ ያጣልና እንጠንቀቅ።ነገር ግን በቅንጅት ወቅት በተሰራበትና በሰራው ማስረጃ ባለው ነገር መኮነን ተገቢ ነው እላለሁ።

ብርሀኑ በመፅሀፉ! ልደቱን እንዲህ ይገልፀዋል።"ጠንቃቃ፣ዓላማውን አሥቀድሞ ያሠላ የብልጠት አካሄዱ የላቀ..."ይለዋል። ብርሀኑን! በክርክርም፣በኃይለኛ ተናጋሪነትም፣በነገሮች አካሄድና አጣጣልም፣በመልሶች ቅልጥፍናም፣ በወጣትነት ዕድሜው በሚያፈልቃቸው አሥተሳሰቦችም ሊቋቋመው የማይችለውና የሚያንቀጠቅጠው ልደቱ ብቻ እንደነበር ገሀድ ነበር።ልደቱ ክርክሩን እንደጀመረው ቢገፋበት ኖሮ ብርሀኑ ቦታውን ያውቅ ነበር።

ነገር ግን ብርሀኑ የተጠቀመበት ዘዴ ዕድሜውና የተንኮል ልምዱ ከልደቱ በመላቁ፣

(1)የልደቱን በመኢአድ ላይ የሚያደርገውን አላስፈላጊ ዘመቻ እንደቅራኔ መጠቀምንና ለመኢአድ ብርሀኑ መልካም አሳቢ መሥሎ መቅረብን፣ (2)የልደቱን ታዋቂነት እየተከታተለ ማራከስን፣ (3) ልደቱ "ሕዝቡ ያለመሪ ለሰላማዊ ትግሉ አደባባይ ሲወጣ እንምራው"ሲል ብርሀኑ "እንደራደራለን" ብሎ ማክሸፉን ወዘተ፣ ተያያዘው።

ከሁሉም በላይ ግን ኢዴፓ-መድህን የመረጠውና የላከው ልደቱን እንደሆነና ሁለተኛው ፓርቲ መሆኑ እየታወቀ፣እርሱ እንዳይሆን መደረጉ ከምንም በላይ አቃጥሎታል።"ኢዴፓ-መድህን ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርነቱን ዶክተር ኃይሉ አርአያ ተመርጦ ቢመጣ ይሠጠው ነበር፣ልደቱ ተመርጦህ ሥለመጣህ አይሠጥም "ዓይነት አሠራር ሎጂክን ያልተከተለ እንደሆነ ሲረዳ እና የቀድሞ ተሰሚነቱና ዝናው ሲጠፋ "ቆይ አሳያችኋለሁ"በሚል ዛቻ መነሳት የግልን ሥልጣን፣ክብርና ዝና ከማሥቀደም የመጣ ትንሽነት ከመሆን አይዘልም።ማድረግ የነበረበት አርቆ በማሰብ አሠራሩ ትክክል አለመሆኑን እየተናገረ ለማሻሻል መጣርና አብሮ መጓዝ፣የብርሀኑንና መሰሎቹን ተልዕኮ በሚችለው ማጋለጥ፣ከመኢአድ ራስ ላይ መውረድ ነበር።አለበለዚያ አርፎ መቀመጥ ነበረበት።

ክፍል6

ልደቱ!በብርሀኑ ሲሸነፍ የወሰደው እርምጃ ግን አርቆ ማሰብ የተሳነው፣ከአፍንጫ ሥር አሥተሳሰብ በመነሳት "ማህተም አላሳርፍም" ከማለት ባሻገር ጠቅልሎ ወያኔ ፓርላማ ውስጥ መሸጎጡ ነገሩን ሁሉ አበላሸው።

ብርሀኑም ልደቱን ማኖ ካስነካ በኋላ የቅንጅት ጀግና መስሎ በመቅረብ የለመደውን ማተራመስ ቀጥሎበታል፣ያልገባው ሲከተለው፣የገባው ዓይንህ ላፈር ብሎታል።ያም ሆነ ይህ ቅንጅትን
መቀመቅ እንደከተተው ይታወቃል።ከዚያም በኋላ መኢአድ በኢንጂንዬር ኃይሉ አመራር እንደገና ለማገገም ችሎ ነበር።
ህብረትና ቅንጅት የምርጫውን መጭበርበር አሥመልክቶ መሥከረም 23ቀን የሚጀመር የ3ቀናት የቤት ውስጥ መዋል ጥሪ አደረጉ።ይህንን የአሜሪካ ኤምባሲ ሲሰማ ለማሥተጓጎልና ለማክሸፍ መስከረም 21ቀን ሥብሰባ ጠራቸው።
ልብ በሉ ብርሀኑ "ለአዲስ አበባ ከንቲባነት ተመርጫለሁ" በሚል፣ በአሁኑ የቅንጅት አመራር ውስጥ ግን ብርቱካንንና ኢዮኤልን ሥላስመረጠ፣ኢንጂንዬር ኃይሉም ከህመሙ ጋርም ሥለሚታገል ቅንጅትን ብርሀኑ በተዘዋዋሪ እንደሚመራው እርግጠኛ ነበር።
የወያኔ ነጮች እንደልማዳቸው አድማውን ለማክሸፍ፣ የአሜሪካ አምባሳደር ቪኪ፣ከ3ቱ የአውሮፓ ህብረት አምባሳደሮች ጋር ብርሀኑን ጠርታ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተቃዋሚዎች የሚጠበቀው ህገ መንግሥቱን መቀበላቸውን ማረጋገጥና የጠሩትን የቤት መቆዬት አድማ ማንሳት ነው"ሥላለ፣ለማድረግ ያሰባችሁትን " የመንገድ ላይ ነውጥ" ሥለሚለውና የኃይል እርምጃ እንዳይወሥድባችሁ በመሥጋት፣ጧት ቀጠሮ ሥላለኝ ይዠው የምሄድ ነገር ካለ ለመወያየት ነው የጠራኋችሁ አለች።
እነብርሀኑም ሊደረግ የነበረውን "የጠሩትን የቤት መቆዬት አድማ ማንሳታቸውን" ወጥተው በአደባባይ እንደማይደረግ ተናገሩ።ወያኔም ወዲያውኑ በጋዜጣ፣በራዲዮ፣በቴሌቪዥን በራዲዮ ፋናም ቀኑን ሙሉ "ተቃዋሚዎች ወደህሊናቸው ተመልሰውና የአመፅን መንገድ ትተው ወደ ድርድር መጡ" ብሎ ተጠቀመበት።
ይህ ከሆነ በኋላ ውይይቱ ከመለስ ጋር ተጀመረ። መለስም እንደለመደው ፎክሮ "አሁን ሁላችሁም ከዚህ መውጣት ትችላላችሁ፣ይህ ውይይት በዚህ ይበቃል"ካለ በኋላ በአደራዳሪዎቹ ተብዬዎቹ ጣልቃ መግባት ምክንያት ውይይቱ ቀጠለ። እነብርሀኑም ልምምጡን ቀጠሉ። ቀጣዩ ውይይት ከበረከት ጋር ሲካሄድ "ቅንጅቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ድርድሩን የጠየቀው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ነው ላለው ማሥተባበያ ካልሰጠ አንቀጥልም" አለ። ያለጥፋቱ ቅንጅት ማሥተባበያ እንዲሰጥ ተደረገ። ብርሀኑ!ከመለስ ወደበረከት ፣ከበረከት ወደመለስ በመሽከርከር ግልምጫውንና ሥድቡን እየተቀበለ የወያኔን የጊዜ መግዣ ሲያራምድ ቆዬ።ከመለስም ጋር ያው እንደተለመደው ምሱን ቀምሶ በመመለስ "የድርድሩ ውጤት" የሚለውን ማብራሪያ ለቅንጅቱ አቀረበ። በዚህ ጊዜ ብርሀኑ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ስብሰባ እንዲጠራ አድርጎ "ድርድሩ" የደረሰበትን ዋጋቢስ ሁኔታ ይገልፃል። "ኢህአዴግ የቀረቡትን ዋና ዋና ጥያቄዎች በጥቅሉ አልወያይበትም ብሎ መዝጋቱ ቀድሞውንም የቤት መቆዬት ጥሪውን ለማስቆም እንጅ ከልቡ ለመደራደር ፈልጎ ሥላልነበር እሽ ማለት አልነበረብንም የሚል በብርሀኑ ላይ ያነጣጠረ ወቀሳ፣ቁጭትና ንዴት ተንፀባረቀ።ቀደምም ሲል ብርሀኑ "ኢሕአዴግን ያምናል" የሚለው ክስ አሁን ተጠናክሮ መጣ። ከፊሉም እያጉረመረመ "ብርሀኑ ከቅንጅት በላይ ለወያኔ ቆሟል" እሥከማለት ደረሰ።ለማንኛውም ይህ ዓይነቱ ድርድር አከተመ። አሁን ፓርላማ ሥለመግባትና አለመግባት በተመለከተ የላዕላይ ምክርቤቱ ሥብሰባ ተጠራ።ብርሀኑና መሰሎቹ ፓርላማ የመግባቱን ውይይት ወደማጠናቀቁ ደርሰው ነበር።ብርሀኑ ፓርላማ ለመግባት ከነበረው መቋመጥ የተነሳ
"ከዲሞክራሲ ግንባታ መሠረታዊ ሂደት አኳያ የግንቦቱን ምርጫ መጭበርበርን ለዘላቂው ዲሞክራሲ ሥንል ልንተወው እንችላለን" ማለቱም አይዘነጋም ።ፓርላማ ሊገባም ወስኖ ነበር።
በዚህ ጊዜ ሊቀ መንበሩ ኢንጂኔር ኃይሉ ለህክምና አሜሪካ ሥለነበር ከኢትዮጵያውያን ጋር ባደረገው ውይይት፣"ሕዝቡ ፓርላማ አትግቡ" ማለቱን ሥላረጋገጠ፣ቅንጅት ፓርላማ እንደማይገባ ተናገረ።ወዲያውኑ ብርሀኑ "በዜና አቀራረቡ ያለመረዳት ችግር እንዳለ የሚገልፅ ማሥተባበያ አዘጋጅቶ" የኃይሉን ንግግር የሚሽር መግለጫ ከማውጣቱም ባሻገር፣ ለኢንጂንዬር ኃይሉ ደውሎ "ቅንጅቱ ገና አልወሰነም"" ከማለት በሥተቀር ሌላ መናገር እንደሌለበት ጫና ያሥቀመጠበታል።
በዚህ ጊዜ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድረ-ገፆች ከኢትዮጵያን ሪቪው ጭምር "ይህ ቅንጅትን ከውስጥ ሆኖ የሚቦረቡረው የኢሕአዴግ የውስጥ አርበኛ የሆነው የብርሀኑ ሥራ ነው።እንዴት የሊቀ መንበሩን ሃሳብ ተቃርኖ ወሬ ያናፍሳል፣ወዘተ"በማለት የብርሀኑን ምንነት ቀድመው እንደተረዱ ይታወቃል።
ኢንጂንዬር ኃይሉም ከዚህ ሁኔታ በኋላ"የፓርላማን ጉዳይ አሥመልክቶ በሚደረግ ውይይትም ሆነ ውሳኔ መሳተፍ ሥለምፈልግ ትንሽ አዘግዩት የሚል ደብዳቤ ለሥራ አሥፈፃሚው ከላከ በኋላ፣ህክምናውን አቋርጦ ከአሜሪካ በመመለስ የቅንጅቱ ሥብሰባ ተደረገ።ሊቀመንበሩ ሥብሰባው ላይ እያለ ብርሀኑ የተዘዋዋሪ ኩዴታውን አጠናክሮና

ተሯሩጦ፣ብርቱካንን እንድትመራ ያደርጋታል።በኢንጂኔር ኃይሉ ላይ “ብርሀኑ የማሥተባበያ መግለጫ አወጥቶበት፣ሥልክ አሜሪካ ድረስ በመደወል እንዲህ አትበል፣እንዲያ በል ብሎት ፣ እሱ ራሱ ሊቀመንበሩ ሥብሰባው ላይ እያለ፣ተቀዳሚ ምክትሏ ብርቱካን እንድትመራ ወሥኖበት፣ኢንጂንዬር ኃይሉ! ምን ያህል ሆደሠፊና ትልቅ ሠው ቢሆን ነው ይህንን ሁሉ ማሳለፉ? ይህ በዕውነትም የኃይሉን የአመራር ብቃት ያረጋግጣል።

ያም ሆነ ይህ ፓርላማ “እንግባ አንግባ” የሚለው ክርክር ጦፈ።በድርድሩ ወቅት የሪፖርተርን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አማረ አረጋዊን ብርሀኑ ያማከረው እንደነበር ቀደም ሲል ገልጫለሁ።ይህ የቅንጅት ክርክር ቅዳሜ ቀኑን ሙሉ ተደርጎ በማግሥቱ ሊቀጥል ተበተነ ።እሁድ ጧት የሪፖርተር ጋዜጣ ”ብርሀኑና ልደቱ ፓርላማ መግባትን ይደግፋሉ”የሚል የመጀመሪያ ገፅ ዜና ወጣ።እሁድ ክርክሩ ቀጠለ።በዚህ ጊዜ ብርሀኑ አዲስ አበባን ከሌሎቹ ጋር እንዲረከብ የምርጫ ቦርድ ኃላፊ ተስፋዬ መንገሻ ደውሎ መዘጋጃ ቤት ድረስ እንዲሄዱ ይነግረዋል፣ሊረከቡ ሲሄዱ፣ ፓርላማ ካልገባችሁ አትረከቡም ተባሉ። ወያኔ ይህንን በዚች ወቅት ያደረገውና ብርሀኑንም የፈለገው ብዙሀኑን አሳምኖ ፓርላማ እንዲገቡና አዲስ አበባንም ብርሀኑ እንዲረከብ ነበር።ብርሀኑ የቻለውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪም ጥሯል ግን አልተሳካም።ብዙሀኑ ግን “አንገባም” የሚል አቋም ያዘ።በዚህ ጊዜ ብርሀኑ”ኢሕአዴግ ተናካሽ አውሬ”መሆኑን አሥገነዘበ። (1) እነመለስና እነበረከትም ብርሀኑ አብሯቸው ሲሰራ ሥለሚያውቁትና “ተቃዋሚ ነኝ”ካለበት ጊዜ ጀምሮ ሥለራቁትና ፊት ሥለነሱት፣ብሎም “ለድርድር” በሚል በተገናኘ ቁጥር ሥብዕናውን በተደጋጋሚ ሥለነኩት፣ የሕዝቡንም ቁጣና “አትግቡ” የሚለውን ሲመለከትና የቅንጅት ብዙሀኑ “አንገባም” የሚል አቋም ሲይዝ፣ወደፊት ቅንጅትን አዋህዶ በቁጥጥሩ የማድረግ ህልምም ሥለነበረው፣ሳይወድ በግድ “አንግባ” የሚለው ብዙሀን ጋር መቆም ተገደደ። ኢንጂንዬር ኃይሉ

ከአሜሪካ ተመልሶ በስብሰባው ላይ ባይገኝና በአገር አቀፍ ያሉትን የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ባያሳትፍ “አንገባም” የሚለው “እንገባለን” በሚለው ቀደም ብሎ ሊፈፀም በቻለ ነበር።

ሰኔ አንድ(1)ቀን በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተጀመረው የሠላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ሕዝቡ በወያኔ አልሞተኳሾች ጭንቅላቱንና ደረቱን በጥይት እየተመታ እንደወደቀ ይታወቃል።

ጥቅምት 21ቀን ቅንጅቱ! በአደባባይ ሠላማዊ ሠልፍ ለመውጣት ሳይሆን፣ በኢኮኖሚ ማዕቀቦችና በግማሽ ሰዓት የጥሩንባ ማሰማት ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ “የቤት ውስጥ የመቆዬት አድማ” ላይ እንዲደርስ የጠራው ጥሪ፣ጥቅምት 22ቀን በወያኔ ግጭት ፈጣሪነት የጥሩንባ ማሰማት ደረጃ ላይ እያለ በአጭር ተቀጨ። ከየመንገዱና ከመንደሮቻቸው ግለሰቦችንና የቅንጅትን አባላት በብዛት እየለቀሙ አሰሩ።

ብርሀኑ እንዲህ ይገልፀዋል (1) “ ሸከሙን መንግሥት ላይ ብቻ በመጣል ልናልፈው አንችልም።ትግሉን በሚያካሂዱት ኃይሎችም ዘንድ የትግሉን ይዘት ሙሉ ለሙሉ ያለመረዳት ችግር ነበር” ብሎ ሕዝቡን ኮንኗል።

(2) “ኢሕአዴግ በጥላቻ ሲያጠቃን፣እኛ ፍቅር ይዘን እንቀበለው። ሕዝቡ ራሱን እንኳን ከጥቃት ሲከላከል በተቻለው መጠን አጥቂውን(ወያኔን ማለትም ብርሀኑ ኢሕአዴግ እያለ የሚያቆላምጠውን ) እንዳይጎዳ መሞከር ይጠበቅበታል።ሥለዚህም አጥቂው ላይ ጥላቻ የለበትም”ይለናል።

ወያኔ ምርጫውን ሳያሸንፍ “አሸንፌአለሁ” ብሎ ካወጀ በኋላ፣የአወጀውንም እንደማይቀይር በእርግጠኝነት እየታወቀ፣ሕዝቡም በአልሞ ተኳሾች ጭንቅላቱንና ልቡን እየተመታ ሲወድቅ፣ብርሀኑና መሰሎቹ መድረኩን በመቆጣጠራቸው “የምርጫ ሂደት ውይይቶች ከኢሕአዴግ ጋር” በማለት ከግንቦት7ቀን እሥከ ጥቅምት 21ቀን ድረስ ሞከረውት ከከሸፈና ተሚጦ ካለቀ በኋላ፣ገና በግማሽ ሰዓት የጥሩንባ ማሰማት ደረጃ ላይ ባለ ነገር ፣በሰዎች ላይ ግፍ ሲፈፀም ከጎናቸው እንደመቆም፣ ወያኔ ሲገላችሁ፣ሲደበድባችሁ ዝም ብላችሁ እለቁ፣”ቀኝህን ሲመጣህም ግራህን ሥጠው” ዓይነት አባባል አሥገራሚ ነው።ወያኔን ከመኮነንና ከማውገዝ ይልቅ “በወያኔ ላይ ክንድህን አላላ” ዓይነት ሠበካ መሠንዘር ጥቅሙ ለማን ነው? ይህ ነው የዛሬው የግንቦት7 ፋኖ ወኔ!

ያም ሆነ ይህ ኃይሉ ሻዎል ከአሜሪካ ሲመጣ ሁኔታው ተቀይሮ ቅንጅትም ወደ ወያኔ ፓርላማ ሳይገባ ቀረ።ይህ ብርሀኑን አናደደ፣ቀጥሎም ከጥቅምት 22ቀን ጀምሮ ለዕሥር ተዳረጉ።ብርሀኑ!ከወያኔ እሥር ቤት ውስጥ መፅሐፍ መፃፍ መቻሉ አጠያያቂ ቢሆንም እሥር ቤት በነበረበት ጊዜ መፅሐፍ ፅፎ እንደወጣ ነግሮናል። ከእሥር ሊወጡ ሲሉ” ጥፋተኛ ነኝ” ብለህ ፈርም ሲባል ተሽቀዳድሞ የፈረመው እሱ እንደነበር ይነገራል፣እሱም አይክድም።

ከእሥር እንደወጡም የኢንጂንዬር ኃይሉ ህመሙ ጠንቶበት ሥለነበር፣ ወደነበረበት ሆስፒታል ወደአሜሪካ ለመሄድ ለቪዛ ቀድሞ አሥገብቶ እየተጠባበቀ እያለ፣ከእሱ በኋላ ያመለከቱት ብርሀኑና ብርቱካን ቀድመው ቪዛ አግኝተው አሜሪካ ሄደው ነግግር በማድረግ ሠው እየከፋፍሉ “ቅንጅትን” ሲበልቱት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። የአሜሪካ አምባሳደር

ወይዘሮ ቪኪ

በይሥሙላው ድርድር ምክንያት ከብርሀኑ ጋር እጅና ጓንት ለመሆን ሥለበቁ እንዲህ መደረጉ አይደንቅም።የኃይሉም ቢዘገይም ተሳክቶ አሜሪካ ለመሄድ በቅቷል።

ይህ በዚህ እንዳለ እነብርሀኑ ወደአሜሪካ ሲሄዱ፣የከምባታው ኪስ አውላቂና ገንዘብ ዘራፊው ኢዮኤል ወደአውሮፓ የመጣውን ቡድን ይዞ እየዞረ በቅንጅት ሥም ገንዘባችንን ከግብረአበሮቹ ጋር ገፎ ሄዶ ለብርሀኑ አሥረክቧል። አሁንም ከብርሀኑ ጉያ እንደተሸጎጠ ነው።ይህ በቅንጅት ሥም ከአሜሪካም ከአውሮፓም በአጠቃላይ ከዓለም አቀፍ የተሰበሰበው ገንዘብ፣እነብርሀኑ የዘረፉን እንደሆነ መታወቅ አለበት።ምክንያቱም በዕለቱ ለግሠን፣በማግሥቱ ሲገባን፣እነብርሀኑ የእነኢንጂነር ኃይሉን አመራር የካዱት ከእሥር ሲወጡ ሆኖ ሳለ፣ጠቀም ያለ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚያዋጣቸው፣የኃይሉን ሥም በመጠቀም እንደሆነ ሥለተገነዘቡት፣"ኢንጂኔር ኃይሉ የቅንጅቱ መሪያችን ናቸው፣እያሉ እየዋሹ ነበር፣አባላቱና ደጋፊውን የዘረፉት።ብርቱካንማ "ጋሽ ኃይሉ" እያለች በለሰለሰ አንደበት ሥትቀላምድ ዕውነት ታስመስል ነበር።

ብርሀኑ!ከእሥር ሲወጣ መጀመሪያ ያደረገው ነገር ቢኖር፣ብርቱካንን አሥከትሎ የመኢአድንና የኢዴፓ-መድህንን አመራር በአሉባልታና በተለያዩ መንገዶች ጠለሸት አልብሶና አሸቀንጥሮ በመጣል፣ያ ፀረ-አማራነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣በቅንጅት ሥም አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ወደራሱ ለመጠቅለል እንደነበር በቅንጅት የመለያያ ዘመናቸው በተግባር ያየነው ጉዳይ ነው።በከፊልም ተሳክቶላቸው፣ከመኢአድም ከኢዴፓ-መድህንም ሠዎች አሥከድተዋል።ድርጅቶቹንም አዳክመዋል።ከአፈረሱት መካከል ብርሀኑ በግምባር ቀደም የሚጠቀስ ነው።

ቅንጅት ሲፈጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሥታውን አበሠረ፣ሁሉም ፈነደቀ።ነገር ግን ያ ደስታና መፈንደቅ እያደር በእነብርሀኑ አሻጥር መቀመቅ ወረደ።የብርሀኑና የመሰሎቹ መሠሪነት ሥር የሰደደ በመሆኑ፣ገና ከጅምሩ ተንኮል አዝለው እንደተቀላቀሉ እነመኢአድና ኢዴፓ-መድህን ባለመረዳታቸው የሥንት ሚሊዮን ሕዝብ ተስፋ የነበረው ቅንጅት እንዳልነበር ሆኖ ቀረ።

ሞት ለሕዝብ ጠላቶች

ድል ለሕዝብ

በላይ ደጀኔ

ከዚሕ በፊት የተጻፈውን ለማንበብ ይህን ይጫኑት

**http://www.ethiopanorama.com/wp-content/uploads/2017/09/G7-neberku-20170421.pdf**